አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3595 ቅዳሜ ጥቅምት 7 ቀን 2019 ዓ.ም ዋጋው 10.00 ብር

ትልቅ ሀገር ፣ ትልቅ ህዝብ ፣ ታላቅ ርዕይ!!

የማይበገረው የድል ጉዞ

- ኢትዮጵያ ጠላቶች ተደራራቢ ፈተናዎችን ቢደቅኑባትም ሴራዎችን በማክሸፍ ወደ ላቀ ስኬት በመሸጋገር ላይ እንዳለች ተጠቁሟል

በመለሰ ተሰጋ

የኢትዮጵያ ታሪክ ረጅም፣ ጥልቅና ዘመናትን የተሻገረ በፅናትና በነፃነት ተጋድሎ የተዋዛ ነው። ሀገሪቱ በረጅሙ የታሪክ ሂደቷ ውስጥ በርካታ ውስብስብ ፈተናዎችን፣ የወረራ ሙከራዎችንና የውስጥ ሽኩቻዎችን አልፋ ዛሬም በከፍታው ማማ ላይ ቆማለች። የታሪክ ድርሳናት እንደሚመሰክሩት የኢትዮጵያ የሀገርነት ህልውናና የሉዓላዊነት ምስጢር በቀጣናዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚለዋወጡ የኃይል ሚዛኖች ውስጥ የራሷን ነፃነት የመጠበቅና የመከላከል የረጅም ዘመናት ተቋማዊና ህዝባዊ ባህል በመገንባቷ ላይ የተመሠረተ ነው።

ይሁን እንጂ የእነዚህ ሁሉ ታሪካዊ ክስተቶች ምስጢር በጥንቃቄ ሲፈተሽ ብቅ የሚል አንድ ግልጽ እውነታ አለ፤ ኢትዮጵያ በውስጥ ሰላሟ ተረጋግታ፣ የአንድነት መንፈሷ ተጠናክሮ፣ በልማት ጎዳና ላይ ሳትወላውል መራመድ ስትጀምር፣ እንዲሁም በክፍለ-አህጉራዊና በአህጉራዊ አውዶች ላይ ያላት ተፅዕኖ ፈጣሪነትና ተደማጭነት ሲያይል፣ የቅርብና የሩቅ ጠላቶቿ ከተደበቁበት ጉድጓድ ይወጣሉ። ይህ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚከሰት አጋጣሚ ሳይሆን፣

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

ፎቶ:- ከገጸ ድር
ኢትዮጵያ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶች ሴራዎች ቢደራረቡባትም በፅናት አልፋ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስከብራ ትኖራለች

ለንግዱ ማህበረሰብ ዘመናዊ አገልግሎት ለማቅረብ ምን እየተሰራ ነው?

6

ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ

በጥበብ የተሸመነው ወርሃ ጥቅምት

11

ፎቶ- ከገፀ ድር
ጥቅምትን በጥበብ ከሸመኑት መካከል ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን እና ድምጻዊ ነዋይ ደበበ ተጠቃሽ ናቸው

አፍሪካ በአዳዲስ የስፖርት ምዕራፎች

20

ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ
በሌላው ዓለም በስፋት ይካሄዱ የነበሩ የስፖርት ውድድሮች ወደ አፍሪካ መምጣት ጀምረዋል

የአፍሪካ የለውጥ ብርሃን

- አዲስ አበባ ለአፍሪካ ከተሞች ሁለንተናዊ ተምሳሌትነቷን አጠናክራ መቀጠሏ ተመላክቷል

ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች አመራር ኢኒሼቲቭ የ2026 የአመራሮች ፎረም ተሳታፊዎችን በተቀበሉበት ወቅት

በመለሰ ተሰጋ

አዲስ አበባ በ1879 ዓመተ ምህረት በእንጦጦ ተራራ ሥር ስትመሠረት፣ ለቦታው መመረጥ ዋና ምክንያቶች የፍል ውሃው መኖር፣ መልካም የአየር ጠባይ፣ የደን ሀብትና ስትራቴጂካዊ አቀማመጧ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ።

ይህ ውሳኔ በዘመኑ ብልህ አካሄድ ቢሆንም አመሠራረቷ ግን በወቅቱ የነበሩትን የከተማ ፕላን መርሆዎች ተከትሎ ባለመሆኑ ከተማዋ በዘመናዊ ማስተር ፕላን ሳይሆን በመኳንንት ሰፈር፣ በገበያዎች፣ በቤተ መንግሥትና በቤተ እምነቶች ዙሪያ በተፈጥሯዊ ሁኔታ እያደገች እንድትሄድ አድርጓታል።

እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢልት

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የቅጠል ተራ ሁለት መልኮች

በለይላ መሀመድ

“ያደግንበት ሰፈር ልጅነታችንን ነጥቆናል ማለት እችላለሁ” ሲል በቁጭት ይናገራል፤ የ24 ዓመቱ ወጣት በድሉ አሸናፊ የትናንት ሕይወቱን ሲያስታውስ። ወጣቱ ተወልዶ ያደገው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መርካቶ አካባቢ በተለምዶ ቅጠል ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። ሰፈሩ መጫወቻ እና አረንጓዴ ስፍራ እንዲሁም መኪና እንኳን በነፃነት የሚገባበት መንገድ አልነበረውም።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል


የትውልድ ድምፅ
VOICE OF GENERATION
Addis Media Network-AMN
Addis Media Network-AMN
Addis Media Network-AMN
Addis Media Network

አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

ርዕሰ አንቀፅ

የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ የብሔራዊ ደህንነቷ ጉዳይ ነው!

የምንገኝበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና በታላላቅ የተፈጥሮ እድሎች፣ በሰፊ የንግድ መስመሮችና በደመቀ ባህላዊ ብዝሃነት የተሞላ የመሆኑን ያህል፣ በርካታ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች ያሉበት ነው። በዚህ እጅግ ወሳኝ ስትራቴጂካዊ ስፍራ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ የቀጣናው ዘላቂ ሰላም፣ መረጋጋትና የጋራ እድገት ዋና አምድ ሆና ስትሰራ ቆይታለች። ሆኖም ይህች ታላቅ ሀገር ከቀይ ባህር ካላት ቅርበት፣ ታሪካዊ ትስስርና ዓለም አቀፋዊ ህጎች አንጻር የባህር በር አልባ ሆና እንድትቀር መደረጓ ተገቢነት የሌለውና ቀጣናዊ ትስስርን ሙሉ ለማድረግ እንቅፋት የሆነ ጉዳይ ነው። የባህር በር ጥያቄው የብሔራዊ ደህንነትና የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ይህንን እውነታ መረዳትና ማስተካከል ደግሞ የሁሉም ወገን ጥረት መሆን አለበት።

ኢትዮጵያ ሰፊ የወጪ ገቢ ንግድ ያላት ሀገር እንደመሆኗ በባህር ደህንነት ላይ የጎላ ሚና ያላት ሀገር መሆን ይገባታል፤ እስካሁን ባከናወነቻቸው ግዙፍ የልማት ስራዎች የቀጣናውን ሀገራት በተግባር ማስተሳሰር ችላለች። በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሱዳንን፣ ጂቡቲንና ኬንያን ከራሷ ጋር አስተሳስራለች። በተጨማሪም ድንበር ተሻጋሪ የመንገድ መሰረተ ልማቶችን በመገንባትና የንግድ እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት የምስራቅ አፍሪካን የኢኮኖሚ ውህደት እውን ለማድረግ የፊት አውራሪነት ሚናዋን እየተወጣች ትገኛለች። ከኢኮኖሚ ትስስር ባሻገር፣ ኢትዮጵያ በቀጣናው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማረጋጋትና ዘላቂ ሰላምን ለመገንባት በግንባር ቀደምትነት ስትሰራ ቆይታለች። በተለይም በሶማሊያና በደቡብ ሱዳን ከተካሄዱት ሰላም የማስከበር ተልዕኮዎች ጀምሮ እስከ ቀጣናዊ የሰላም ድርድሮች ድረስ የከፈለችው መስዋዕትነትና የተወጣችው ኃላፊነት ግዙፍ ነው። አሸባሪነትን በመከላከልና የህዝቦችን ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ያበረከተችው አስተዋፅኦ የቀጣናውን ሰላም አፅንቶ ለማቆየት ያስቻለ ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ተግባር ነው።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ይህንን ሁሉ ታላቅ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነት እየተወጣች ያለችው ቀጥተኛ የመተንፈሻ የባህር በር ሳይኖራት መሆኑ አሳዛኝ እውነታ ነው። የባህር በር አለመኖር በሀገሪቱ የገቢና ወጪ ንግድ ላይ የሚያስከትለው ከፍተኛ ወጪና የሎጂስቲክስ ጫና፣ የኢኮኖሚ እድገቷን ከመግታት አልፎ የቀጣናውን አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ ፍጥነት ያዘገየዋል። ይህንን ጫና በመቅረፍ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የምትሆንበትን አዎንታዊና ህጋዊ መንገድ መፍጠር፣ ሀገሪቱ ያላትን ሙሉ አቅም ተጠቅማ ለቀጣናው የሚኖራትን የአበርክቶ መጠን ያሳድገዋል። ይኸን ጥያቄዋን በሰላማዊ፣ በሰጥቶ መቀበልና በዲፕሎማሲ ማሳካት ትፈልጋለች፡፡

ስለሆነም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፣ የልማት አጋሮችና ጎረቤት ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ግንኙነት ይህንን ሀገራችን ያላትን ወሳኝ ቀጣናዊ ሚና ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት የምታደርገው ጥረትና ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት የምታቀርበው ጥያቄ፣ የቀጣናውንና የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ዘላቂ የንግድና የደህንነት ጥያቄዎች የሚመልስ ነው። የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ፍትሐዊና አዎንታዊ መልስ እንዲያገኝ የሚደረግ የማንኛውም አካል እገዛና ትብብር ከኢትዮጵያ አልፎ ለጠቅላላው የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ብልፅግና እጅግ ወሳኝ ነው። ኢትዮጵያ በጠነከረችና በበለፀገች ቁጥር የቀጣናው ሰላም፣ ንግድና ስልጣኔ የዚያኑ ያህል ይጎለብታል። በመሆኑም የባህር በር ጥያቄዋ መመለስ የቀጣናውን የጋራ ተስፋ እውን የሚያደርግ፣ የቀይ ባህርን አካባቢ የሰላምና የንግድ ቀጣና የሚያደርግ ትልቅ በረከት መሆኑን ተረድቶ በጋራ መስራት የዘመኑ ታላቅ ጥሪ ነው።

የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

የጋራ ጥረት የሚሻው የችግኝ ክብካቤ

ኦልቢራት ከኮተቤ

ባለፈው የክረምት ወቅት መላው ህብረተሰብ በተለየ ተነሳሽነትና የባለቤትነት ስሜት በመንቀሳቀስ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን ተክሏል። ተራራዎች፣ የመንገድ ዳርቻዎች፣ የሕዝብና የግል ተቋማት ግቢዎች እንዲሁም ክፍት መሬቶች በሙሉ አረንጓዴ ለብሰዋል። በ2011 ዓ.ም የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የሀገር በቀል እጽዋቶችንና የተፈጥሮ ሀብቶችን ከመጠበቅ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመከላከልና የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ያለው አስተዋፅኦ እንደቀላል የሚታይ አይደለም፡፡

መርሃ ግብሩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2018 ዓ.ም የክረምቱ ወቅት ድረስ 48 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል የሀገሪቱን አረንጓዴ ሽፋን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል። የኢትዮጵያ አረንጓዴ አሻራ ልማት ከተፈጥሮ ኃብት ጥበቃ ባለፈ ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞችን የሰነቀ ሲሆን የአየር ንብረት ተጽዕኖን በመቀነስ ለኢትዮጵያ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ መስኮች ዘርፈ-ብዙ ፋይዳ እያስገኘ ይገኛል፡፡ ይህ ታሪካዊ የህዝብ ንቅናቄ ሀገራችንንና ከተማችንን ወደ ተፈጥሯዊ ለምለምነቷ ለመመለስ የተጣለ ትልቅና ጠንካራ መሠረት ነው። ይሁን እንጂ ይህን መሰረታዊ ስኬት አስጠብቆ ዘላቂ ውጤት ማምጣት የሚቻለው የተተከሉትን ችግኞች በበቂ ሁኔታ መንከባከብና ማሳደግ ሲቻል ብቻ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል።

ችግኝ መትከል የተጀመረው ታላቅ የልማት ጉዞ የመጀመሪያው ምዕራፍ እንጂ የመጨረሻው ማጠቃለያ አይደለም። አሁን የክረምቱ እርጥበት አልፎ ወደ በጋው የፀሐይና የደረቅ አየር ወቅት እየገባን በመሆናችን፣ ችግኞች ከፍተኛ የውሃ እጥረትና የድርቅ አደጋ ያጋጥማቸዋል። በዚህ ወቅት የተተከሉትን ጥቁር አፈር የወረሱ አበቦችና ችግኞች በጥንቃቄ ካልተያዙ፣ በክረምቱ የፈሰሰው ጉልበት በከንቱ ይቀራል። ስለሆነም በበጋው ወቅት ችግኞችን ከድርቅና ከአየር ንብረት ጫና መጠበቅ ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት የሚሻ ወቅታዊ ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ።

በክረምቱ ወቅት ችግኞችን በመትከል፣ በመከታተልና በማጽደቅ ረገድ በርካታ የመንግሥት መዋቅሮች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የትምህርት ተቋማትና የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች በቃልም በሰነድም ኃላፊነት ወስደዋል። ነገር ግን ቃል መግባት ብቻውን ችግኝ የሚያጸድቅ ተአምር ሊፈጥር አይችልም። የተገባው ቃልና ውል ወደ ተግባር ተተርጉሞ፣ መደበኛ የውሃ ማጠጣት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፣ የጥበቃ ሥራዎችን በማጠናከርና ተቋማዊ የባለቤትነት ስሜትን በመተግበር መረጋገጥ አለበት። ተቋማት የተከሏቸውን ችግኞች በየጊዜው እየጎበኙ ውሃ የማጠጣትና የመንከባከብ ግዴታቸውን በቁርጠኝነት መወጣት ይኖርባቸዋል።

ከተቋማት ቁርጠኝነት ጎን ለጎን የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎና ባለቤትነት ለስኬቱ ወሳኝ ነው። በበጋው ወቅት ከብቶችና ሌሎች እንስሳት ገና ያልጠነከሩትን ችግኞች እንዳይበሏቸው፣ እንዳይረግጧቸውና እንዳያበላሿቸው ከወዲሁ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል እላለሁ። በየአካባቢው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አረንጓዴ ልማቱን እንደ የራሳቸው ሀብት በመቁጠር፣ ችግኞችን በጋራ በጥንቃቄ ሊንከባከቧቸውና ከእንስሳት ንክኪ ሊጠብቋቸው ይገባል።

የተተከሉ ችግኞች የዛሬው አካባቢ ውበት ብቻ ሳይሆኑ የነገው ትውልድ ሀብት፣ የንጹህ አየር ምንጭ፣ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከያና የዘላቂ ልማታችን ዋስትና ናቸው። በክረምቱ ወቅት በብዙ ድካምና ወጪ የተተከለ ችግኝ በበጋው ድርቅና በእንስሳት ጥፋት ምክንያት ሳይደርቅና ሳይበላሽ አድጎ ጥላና ፍሬ እንዲሰጥ፣ እያንዳንዱ ዜጋና ተቋም የየድርሻውን ኃላፊነት በቁርጠኝነት መወጣት ይኖርበታል።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

አድራሻ
አምስት ኪሎ ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት
ስልክ 0111 - 112218

አታሚ
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ግራፊክስ ዲዛይን
እዮብ ተፈራ

ሌይአውትና ዲዛይን
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

የእርምት ባለሙያ
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

የዕለቱ አዘጋጆች
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ
ለይላ መሀመድ

ዋና አዘጋጅ
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

ም/ዋና አዘጋጅ
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

ከፍተኛ አርታኢያን
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

የማይበገረው... ከገጽ 1 የዞረ

ፎቶ:- ከገጸ ድር

ኢትዮጵያ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶች ሴራዎች ቢደራረቡባትም በፅናት አልፋ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስከብራ ትኖራለች

በታሪክ ሂደቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የታየና ዛሬም ድረስ የሚታይ መዋቅራዊ የጂኦ-ፖለቲካ እውነታ ነው።

እዚህ ላይ ሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብቷን በራሷ አቅም መጠቀም ስትጀምርና ችግሮቿን በሰለጠነ መንገድ ለመፍታት ስትጥር፣ ጠላቶቿ ለምን ይነሳሉ? ለምንስ ይሰባሰባሉ? የሚለውን ጥያቄ ከሀገሪቱ የታሪክ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እውነታዎች አንጻር መተንተን አስፈላጊ ይሆናል። በዓለም አቀፍ ግንኙነት የ'እውነታዊነት' (Realism) ንድፈ-ሐሳብ እንደሚያስረዳው፣ ሀገራት በዓለም አቀፍ አደባባይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በዋናነት በብሔራዊ ጥቅም እና በኃይል ብልጫ ፍለጋ የሚመራ ነው። ሀንስ ሞርገንታው እ.ኤ.አ በ1948 “Politics Among Nations” በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቁት መጽሐፋቸው እንደሚገልጹት፤ ሀገራት ሌሎች ሀገራት የሚያሳዩትን የኃይልና የሀብት እድገት እንደራሳቸው የህልውና ስጋት አድርገው የመመልከት ተፈጥሯዊ ባህሪ አላቸው።

ኢትዮጵያም የታደለችውን የተፈጥሮ ፀጋ፣ በተለይም የዓባይ ወንዝን፣ ለሀገራዊ ልማቷና ለሕዝቦቿ ብልፅግና ማዋል ስትጀምር፣ በቀጣናውም ሆነ ከቀጣናው ውጭ ያሉ ስግብግብ ኃይሎች በከፍተኛ ሥጋት ይዋጣሉ። ለምሳሌ፤ የግብፅ የዘመናት የውጭ ፖሊሲ በዋናነት የተገነባው የዓባይን ወንዝ በብቸኝነት በመቆጣጠርና የላይኞቹን የተፋሰስ ሀገራት በድህነት፣ በደካማ የመንግሥት መዋቅርና በግጭት ውስጥ አጥምቆ በማቆየት ላይ ነው።

ኢትዮጵያ ይህንን የቆየ ኢ-ፍትሐዊ አሰራር በመስበር፣ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ያሉ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶችን በራሷ አቅም መገንባት ስትጀምር፣ የግብፅና የመሰል ኃይሎች የቆየ የስግብግብነትና የብቸኝነት ፍላጎት ይናጋል። ሀገሪቱ ከጥገኝነት ተላቅቃ በኢኮኖሚ ዋልታዎቿ ሚዛኗን ጠብቃ በራሷ እግር ስትቆም፣ እነዚህ አካላት የራሳቸውን አግላይ የሆነ መሻት ስለሚያጡ፣ የኢትዮጵያን ጉዞ ለማደናቀፍ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ። ናይጄሪያዊው የአፍሪካ ጂኦ-ፖለቲካ ተመራማሪ ፕሮፌሰር አደባዮ አደዴጂ የአፍሪካ ሀገራት የተፈጥሮ ሀብታቸውን በራሳቸው የመቆጣጠርና የመጠቀም መብታቸውን ሲያረጋግጡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የኃይልና የኢኮኖሚ አሰላለፍ የመቀየሩ ጉዳይ አይቀሬ መሆኑን በተለያዩ የፖሊሲ ሰነዶችና መጻሕፍቶቻቸው አብራርተዋል።

ሌላው ኢትዮጵያ ለጥቁር ሕዝቦችና ለመላው አፍሪካውያን የምታስተላልፈው መልዕክት ከጂኦ-ፖለቲካዊ ድንበር በላይ የሰፋ ነው። በ1888 ዓ.ም የተቀዳጀችው ታሪካዊው የዓድዋ ድል፣ በአፍሪካውያን ዘንድ ታግሎ የማሸነፍ ወኔ እንዲነግስና የነፃነት ፀሐይ በአህጉሪቷ ሰማይ ፈክታ እንድትወጣ እንዳደረገ ሁሉ፣ ከድሉ ማግስትም የፓን-አፍሪካኒዝም መንፈስ እንዲያንሰራራ ትልቅ መነሻ ስለመሆኑም ታሪክ ምስክር ነው። ታዋቂው የካሪቢያን የታሪክና የፖለቲካ ምሁር ሲ.ኤል.አር. ጄምስ “A History of Pan-African Revolt” በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለፁት፤ የዓድዋ ድል የነጭ የበላይነትን ስነ-ልቦናዊ ግንብ ያፈረሰና የመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ምልክት ሆኖ በዓለም አቀፍ አደባባይ ላይነቀል የተተከለ ዓርማ ነው፡፡

ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ ከተጠናከረች፣ መላው የአፍሪካ ቅርፅ በአንድነት፣ በነፃነትና በልማት እንደሚለወጥ የውጭ ኃይሎች ጠንቅቀው ያውቃሉ። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብቃት፣ ጀግንነትና የመንፈስ ጥንካሬ ሲግል፣ የቀጣናውንና የመላውን አህጉር ሕዝቦች የሚያነቃቃ ኃይል ይኖረዋል።

ይህ ደግሞ ቀጣናውን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚፈልጉ እንደ ግብፅ፣ እንዲሁም የቀጣናውን ሰላምና መረጋጋት የማይሹ እንደ ሻዕቢያ ያሉ ስግብግብና አግላይ አካሄዶችን ስለሚያከስም፣ ኢትዮጵያ በጠነከረች ቁጥር ዓይናቸውን በጨው አጥበው ለመነሳት ይፈራገጣሉ። ኢትዮጵያ በቀጣናው ጠንካራና ዴሞክራሲያዊት ሀገር ሆና መውጣቷ ለእነዚህ አምባገነንና አግላይ ኃይሎች ህልውና ቀጥተኛ ስጋት በመሆኑ፣ ሁልጊዜም ኢትዮጵያን ማዳከም የፖሊሲያቸው ዋነኛ አካል አድርገውታል።

ወዲህ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት መጠናከር፣ የሀገር ውስጥ ሰላም መረጋጋትና ሕዝቦቿ ችግሮቻቸውን በሰለጠነ አግባብ በውይይት መፍታት መቻላቸው ለታሪካዊ ጠላቶቿ ትልቅ ሽንፈት ነው። ጠላቶች ሁልጊዜም ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚጠቀሙበት ዋነኛው መሣሪያ የውስጥ ልዩነቶችን ማጋነንና የሀገር ውስጥ ባንዳዎችን ማሰለፍ ነውና።

> “የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጉዞ የሚያሳየን ሀገሪቱ በፈተናዎች ውስጥ አልፋ የምትጸና እንጂ በጠላቶቿ ሴራ የምትወድቅ አለመሆኗን ነው”

በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሳይንስ ትንታኔ በወኪል የሚደረግ ጦርነት ተብሎ የሚጠራው ስልት የሚተገበረው በዚህ መንገድ ነው። ታዋቂው የስትራቴጂ ጥናት ምሁሩ ካርል ቮን ክላውዝቪትዝ “On War” በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለጹት፤ አንድን ሀገር በውጭ ኃይል ብቻ ማሸነፍ ከባድ በሚሆንበት ጊዜ፣ የውስጥ ስንጥቆችን በመጠቀም ማዳከም የመጨረሻው ውጤታማ ስልት ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ወደ አንድነትና ብልፅግና ስትራመድ፣ ጠላቶቿ ከተደበቁበት ጉድጓድ በመውጣት ያረጀና የዛገ ጦራቸውን ይዘው፣ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ያሉ የጥቅም ተካፋይ ባንዳዎችን በገንዘብ፣ በሴራና በፕሮፓጋንዳ በማደራጀት የውስጥ እርስ በእርስ ግጭት እንዲነሳ ይሰራሉ። ዓላማቸውም ሀገሪቱ በውስጥ ችግሮቿ ተጠምዳ የውጭ እድገቷና አህጉራዊ ተደማጭነቷ እንዲቀጭ ማድረግ ነው።

በታሪክ ሂደት ውስጥ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተካሄዱት የወረራ ሙከራዎች፣ የ1928 ዓ.ም የፋሺስት ጣሊያን ዳግም ወረራ እና በየዘመናቱ የተሸረቡ የልዩ ልዩ የውጭ ሴራዎች በሙሉ የኢትዮጵያን አቅምና ወኔ ለመስበር የተደረጉ ነበሩ።

ይሁን እንጂ፣ ኢትዮጵያ በእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ውስጥ አልፋ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስከብራ ኖራለች፤ ትኖራለችም። ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያ የሚያጋጥሟትን የውስጥና የውጭ ተደራራቢ ጫናዎች በፍትሕ አደባባይ፣ በጽናት፣ በዲፕሎማሲና በልማት ስራዎቿ መክታ በማሸነፍ ላይ ትገኛለች። የህዳሴው ግድብ ግንባታ መጠናቀቅ፣ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች፣ የሀገሪቱ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድምፅ ከፍ ማለት ኢትዮጵያ ምንም ያህል ብትፈተን ተንበርክካ እንደማትቀርና ይልቁንም በፈተና ውስጥ አልፋ ከፍ ብላ እንደምትወጣ የሚያስረዱ ሕያው ምስክሮች ናቸው።

ካሳለፍናቸው የታሪክ ምዕራፎች የምንማረው ቁም ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ የወደፊት ዋስትና የሚረጋገጠው በሁለት ዋና ዋና አዕማድ ላይ ነው፤ አንደኛው የውስጥ ብሔራዊ መግባባትንና አሳታፊ የፖለቲካ ስርዓትን በማጠናከር የጠላቶችን መጠቀሚያ ቀዳዳ መድፈን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን የሚያረጋግጡ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በስኬት ማጠናቀቅ ነው። ኢትዮጵያ ይህንም መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ምክክር አድርጋ ችግሮቿን በሰላማዊ እና በሰለጠነ መንገድ እየፈታችና ከህዳሴ ግድብ እስከ ቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ የመሳሰሉ ታላላቅ ልማቶችን እያከናወነች መሆኑ ይታወቃል።

የኢትዮ-አረብ ግንኙነት እና የታሪክ ተመራማሪው አደም ካሚል (ፕሮፌሰር) እንደሚገልፁት፣ የኢትዮጵያ ጽናት የተገነባው በአንድ ዘመን ሳይሆን በብዙ ትውልዶች ተሞክሮ እና ቅብብሎሽ ነው። ይህ ጽናት በጦር ሜዳ ብቻ የሚለካ አይደለም፤ ይልቅ በዲፕሎማሲ፣ በባህልና በማንነት ጥበቃ ውስጥም ከፍ ብሎ ታይቷል። ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር እና በዙሪያዎቿ በነበሯት ወደቦች በኩራት በሚንቀሳቀሱት መርከቦቿ በጥንት ዘመን ከዓለም አስፈላጊ የንግድና የሥልጣኔ ማዕከላት አንዷ ነበረች። ወዲህ ደግሞ ከቀይ ባሕርና ዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ወዝና ለዛ ያላቸው ወዳጆቿን እያበዛች፤ ጥቃቅን ስንጥቆችን እየፈለጉ ሰላሟን ለማደፍረስ፣ ልማቷንም ለማጨለም እንቅልፍ የማይተኙ ጠላቶችንም በተባበረ ብርቱ ክንዷ እየመከተችና እያሳፈረች በታሪክ ምዕራፍ ላይ በከፍታ ቀጥላለች።

አደም ካሚል (ፕሮፌሰር) እንደሚናገሩት፣ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው የታሪካዊ ጠላቶቿ ሴራ ምን ያህል ውስብስብና በየዘመናቱ የነበረ ከመሆኑ በላይ የኢትዮጵያውያንን ብርቱ ክንድ ነው። ለአብነትም በኢትዮጵያ ታሪክ እስካሁን ከጥንት እስከ ዛሬ ባለው ሁኔታ ግብፅ ኢትዮጵያን በጠላትነት የመፈረጅ እንቅስቃሴ ታደርጋለች፤ ከዛም አልፎ ጦር እስከማዘመትም ደርሳለች። ግና በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ብርቱ ክንድ እየተለበለበች ተመልሳለች እንጂ።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጉዞ የሚያሳየን ሀገሪቱ በፈተናዎች ውስጥ አልፋ የምትጸና እንጂ በጠላቶቿ ሴራ የምትወድቅ አለመሆኗን ነው። ታሪካዊ ጠላቶቿ የቱንም ያህል ቢሰባሰቡና የውስጥ ባንዳዎችን ቢጠቀሙ፣ የሕዝቧ የታሪክ ፅናት፣ የነፃነት ፍቅርና የልማት ቁርጠኝነት ሁልጊዜም ያሸንፋቸዋል።

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የመጣው መንግሥት ደግሞ አግላይ የሆነውን የፖለቲካ ሥርዓት በመቀየር በመደመር እሳቤ ኢትዮጵያውያንን በአንድ እያሰባሰበና የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን የሚያረጋግጡ ታላላቅ እና ማርሽ ቀያሪ ልማቶችን እያከናወነ ነው። በዚህ አዋጭ መንገድ በመጓዝም ኢትዮጵያ የጀመረችውን የከፍታና የብልፅግና ጉዞ በማጠናከር፣ የቀጣናውና የመላው አፍሪካ የነፃነትና ዕድገት ፀሐይ ሆና መዝለቋ አይቀሬ ነው።

የአፍሪካ... ከገጽ 1 የዞረ

ኢንቫይሮንመንት (Built Environment) ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) ገለጻ፣ የከተማዋ የመጀመሪያ ዕድገት በሳይንስና በምህንድስና ሕግጋት ላይ ባለመመስረቱ፣ መዲናዋ አሁን ላይ እንደ አዲስ ዳግም ታስባ እንድትገነባ የሚያስገድድ ታሪካዊ ጫና ውስጥ እንድትወድቅ አድርጓታል።

ምክንያቱም በቂ የመንገድ መረብ አለመኖር፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች እጥረት፣ እንዲሁም የሰው ልጅን ክብር የማይመጥኑ ደሳሳ ቤቶች የነበሩበት የቆየው የከተማዋ አደረጃጀት፣ የከተማዋን መሠረታዊ ችግሮች ላለፉት አሥርት ዓመታት አከማችቶት ቆይቷልና።

በመሆኑም ከ2010 ዓመተ ምህረት ወዲህ በአዲስ አበባ የተጀመሩት በርካታ የከተማ ልማት ሥራዎች፣ ከተማዋን ከችግር ተቀባይነት ወደ ቅድመ-ዕቅድ መሪነት ለማሸጋገር የተደረጉ ታሪካዊ ጥረቶችም ናቸው።

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች፣ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት፣ የአደባባይ እድሳትና የዲጂታል አገልግሎት ማስፋፋት የዚሁ አዲስ ምዕራፍ አካላት ናቸው። በከተማ ሳይንስ እይታ ‘ኮሪደር’ ማለት የመጓጓዣ፣ የንግድ፣ ለሕዝብ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በሚውሉ ክፍት ቦታዎችና መሠረተ ልማቶች የተቀናጀ አውታር ነው። በመሆኑም በአዲስ አበባ የታየው የኮሪደር ልማት የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን፣ የመብራትና የውሃ ማስወገጃ አውታሮችን አቀናጅቶ የያዘ በመሆኑ ከዓለም አቀፍ የከተማ ፕላን መርሆዎች ጋር ይጣጣማል።

ይህ የከተማዋ ሁለንተናዊ የውበትና የመሠረተ ልማት ማሻሻያ ደግሞ አዲስ አበባን በቱሪዝምና በኮንፈረንስ ዘርፍ ከአህጉራዊ መሸጋገሪያነት (Transit Hub) ወደ ቀዳሚ መዳረሻነት (Destination) ከፍ አድርጓታል።

የቱሪዝም ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ እንደ አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ እንጦጦ ፓርክ፣ የሳይንስ ሙዚየምና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ያሉ ታላላቅ የቱሪስት ማዕከላት በኮሪደር ልማት በተቀናጀ የመንገድ መረብ በመገናኘታቸው የጎብኚዎችን እንግልት በመቀነስ የቱሪስቶችን የመቆያ ጊዜ ከፍ አድርገውታል።

የአዲስ አበባ ተምሳሌትነት በመሠረተ ልማትና በቱሪዝም ግንባታዎች ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን፣ ከማኅበራዊ ኃላፊነት በላይ ለሆነውና የመደመር ትውልድን ለመገንባት መሠረት ለሚጥለው በሰው ሕይወት ላይ ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ቀዳሚ ትኩረት መስጠቷም ተጠቃሽ ነው። በተለይም በሕፃናት እድገት፣ ደህንነትና ደስተኛነት ላይ ያተኮረው የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም የዚሁ ታላቅ ለውጥ ማሳያ ነው።

ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች አመራር ኢኒሼቲቭ የ2026 የአመራሮች ፎረም ተሳታፊዎችን በተቀበሉበት ወቅት

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ሲጀመር በከተማዋ የነበሩት የሕፃናት መጫወቻ ቦታዎች 11 ብቻ የነበሩ ሲሆን፣ በሦስት ዓመታት ውስጥ ቁጥራቸውን ወደ 6 ሺህ 70 ማሳደግ ተችሏል፤ የሕፃናት ማቆያ ማዕከላትም ከ20 ወደ 1 ሺህ 200 ማደጋቸውን የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባሳለፍነው ማክሰኞ በያዝነው 2019 ዓመተ ምህረት በአንደኛው ሩብ ዓመት የተከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ ይፋ ባደረጉት ሪፖርት ላይ ሰፍሯል።

በእነዚህ ተግባራዊ ስኬትና ተምሳሌትነት ምክንያት አዲስ አበባ በአህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ የተሞክሮ ልውውጥ ማዕከል እየሆነች መጥታለች። ባሳለፍነው ረቡዕም አዲስ አበባ ለሁለተኛ ጊዜ ያስተናገደችውን የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች አመራር ኢኒሼቲቭ (AMALI) የ2026 የአመራሮች ፎረምን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት፣ “አዲስ አበባ ለአፍሪካ ከተሞች ተምሳሌት መሆን ጀምራለች” ብለዋል።

“መድረኩ ልምድ ለመለዋወጥ፣ እርስ በርስ ለመማማርና ከተማዋ እያካሄደች ያለውን የለውጥ ጉዞ ለማካፈል ጠቃሚ ዕድል ፈጥሯል” ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ የከተማዋ የለውጥ ጉዞ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አርቆ አሳቢነትና ለከተማዋ ባስቀመጡት ራዕይ የተቃኘ ስለመሆኑም አፅንኦት ሰጥተዋል።

“ይህንን ራዕይ ወደ ተጨባጭ የልማት ውጤቶች እየቀየርን ነው” ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በትራንስፖርት፣ በቤቶች ልማት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎቶች እና በትውልድ ግንባታ ላይ እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎች የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ስለመቻሉም አብራርተዋል።

“የአዲስ አበባ ተምሳሌትነት የመደመር ትውልድን ለመገንባት መሠረት ለሚጥለው በሰው ሕይወት ላይ ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ቀዳሚ ትኩረት የሰጠ ነው”

“በራሳችን የፋይናንስና የዕውቀት አቅም ላይ ተመሥርተን በመሥራታችን፣ የአዲስ አበባ ተሞክሮ ለሌሎች የአፍሪካና የዓለም ከተሞች ጠቃሚ ትምህርቶችን እያበረከተና አዳዲስ የልማት ዕድሎችን እያመላከተ መሆኑም ያስደስተናል” ብለዋል።

“በተለይም አዲስ አበባን በአፍሪካ ሕፃናትን ለማሳደግ ምርጥ ከተማ ለማድረግ ያለንን ጽኑ ቁርጠኝነት እያሳየን ነው። በሕፃናት እድገት (ECD) ላይ ያተኮሩ ተግባራትን በማጠናከር፣ የሕፃናትን ደህንነት፣ ትምህርትና የወደፊት ሕይወት በከተማችን የልማት አጀንዳ ማዕከል ላይ አስቀምጠናል” ብለዋል ከንቲባ አዳነች አቤቤ፡፡

ከአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች አመራር ኢኒሼቲቭ (AMALI) መሪዎችና የፎረሙ ተሳታፊዎች ጋር በመሆን፣ በከተማዋ በልዩ ሁኔታ የተገነባውንና ለፕሮግራሙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገችው ክብርት ሊዛ ዳዬን መታሰቢያ የተሰየመውን የሕፃናት እንክብካቤ ማዕከል መርቀው ለአገልግሎት ማብቃታቸውንም ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል የናይጀሪያው ምክትል ፕሬዝዳንት ካሺም ሼቲማ እና ልዑካቸው በሳምንቱ መጀመሪያ ቀናት አዲስ አበባን በመጎብኘት በሰፈር ደረጃ የተገነቡ የሕፃናት መጫወቻ ቦታዎችን፣ የማቆያና እንክብካቤ ማዕከላትን፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችንና የጤና አገልግሎት ማዕከላትን በመመልከት ልምድ የተለዋወጡበትን ሁኔታ በአብነት ማንሳት እንችላለን፡፡

ከተማዋም እያስመዘገበች ባለችው አስደማሚ ለውጥ የተለያዩ ሽልማቶችን ማግኘቷም አይዘነጋም፡፡ ለአብነትም ሚላን አርባን ፉድ ፖሊሲ ፓክት የተሰኘና በዓለም አቀፍ ደረጃ የከተማ ምግብና ምግብ ነክ ሥራዎች ላይ በተለያየ መልኩ የሚሠራው ተቋም በየዓመቱ በምግብ ሥርዓታቸው ለሌሎች ተሞክሮ ይሆናሉ ያላቸውን ሀገራት በ6 ዘርፎች እንደሚሸልም ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ 2022 ለ8ኛ ጊዜ ባዘጋጀው ሽልማት፣ አዲስ አበባ እያከናወነች ባለው የተማሪዎች ምገባ መርሐ ግብር ዘላቂ አመጋገብና ሥነ ምግብ በሚል ዘርፍ ከተወዳደሩ 133 ከተሞች ቀዳሚ ናት በማለት እውቅና እንደሰጣትም አይዘነጋም፡፡

ከዚህ ባሻገርም፣ በደቡብ ኮሪያ የተበረከተውና ለከተማዋ አመራር እውቅና የሰጠው የሴኡል ስማርት ከተማ 2024 ሽልማት እንዲሁም ለቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት መሻሻል የተሰጠው “የC40 ከተሞች የብሉምበርግ ሽልማቶች” ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በናይሮቢ ኬንያ በተካሄደው የአፍሪካ ስማርት ከተሞች ኢንቨስትመንት ሰሚት 2024 የተሰጠው የአፍሪካ ምርጥ ስማርት ከተማ ሽልማትም የሚታወስ ሲሆን፣ የመንገድ ደህንነትና ፍጥነት ማስተዳደር ላይ ባስመዘገበችው ውጤት በዓለም አቀፍ የከተሞች የዘርፉ ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ መሆኗ የሚታወስ ነው። ከተማዋ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ የብሉምበርግ ፊላንትሮፒስ የከተሞች ጥምረት አባል ለመሆንም በቅታለች፡፡

እነዚህና መሰል ሽልማቶች በከተማዋ ሁለንተናዊ ዝማኔ ውስጥ እንደ ንጋት ጀምበር በፈኩ ልማቶች የተገኙ ናቸው። ከእውቅናና ሽልማቶቹ ባሻገር ከተማዋ የአፍሪካ ተምሳሌትነቷን አጠናክራ መቀጠሏን የሚጠቁሙ ሲሆን፣ በዚህም አፍሪካውያን ከመዲናዋ ልምድ ለመውሰድ በተለያዩ ጊዜያት ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን ቀጥለዋል፡፡

የውበትና የፅዳት መቅረዝ

- በአዲስ አበባ የተከናወኑ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች ዘመናዊ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ባህል እንዲዳብር ማስቻላቸው ተመላክቷል

በመለሰ ተሰጋ

በታሪክ መዝገብ ላይ በሰፈረው ገናና ክብሯ አዲስ አበባ ዕድሜ፣ ወዝ፣ ለዛ እና ጣዕም ያላት ከተማ ናት። የሀገራችንም ሆነ የአፍሪካ አህጉር የስልጣኔ፣ የነፃነት፣ የአንድነት እና የተስፋ መስኮት ስለመሆኗም ዓለም ደጋግሞ የመሰከረው ሀቅ ነው፡፡

እንደ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞች የሀገራት ልብ ምት፣ የስልጣኔ መግቢያ በር እና የምጣኔ ሀብት ርካብ ናቸው። የከተማ ልማት ምሁሩ ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ግሌዘር "የከተሞች ድል" (Triumph of the City) በተሰኘው ጥናታዊ መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ የከተማ ኑሮ መሻሻል ምርታማነትን፣ ባህልን እና የሰዎችን ደስታ ከፍ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ዛሬ ይህ እውነት በአዲስ አበባ መሬት ላይ በግልጽ እየተረጋገጠ ስለመሆኑም የመዲናዋ ነዋሪዎች ይመሰክራሉ፡፡

ለዚህ ትልቅ ለውጥ መምጣት ቀዳሚው ምክንያት የተከናወኑ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች መሆናቸውን በሜክሲኮና ለገሃር አካባቢ ጎዳናዎች ጽዱና ውብ እንዲሆኑ በየዕለቱ የሚተጉትና ለ14 ዓመታት በፅዳት ሥራ ያገለገሉት ወይዘሮ ኤደን መኮንን አጫውተውናል። ወይዘሮ ኤደን፣ "አዲስ አበባ አሁን ፅዱ እየሆነች መጥታለች፤ በዘፈቀደ መንገድ ላይ ተጥሎ የምናየው ቆሻሻ ቀንሷል፤ ለእኛ ለፅዳት ሰራተኞችም ሥራችን ቀላል ሆኖልናል" ይላሉ።

ቀደም ሲል በአንድ ዙር ከሶስት እስከ አራት ሠራተኞች ሆነው ከሰባት እስከ ስምንት ኩንታል ደረቅ ቆሻሻ ይሰበስቡ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ይህ መጠን ቀንሶ ወደ አንድ ወይም ሁለት ኩንታል ዝቅ ብሏል። የፍሳሽ ቱቦዎች በመሸፈናቸው እና ህብረተሰቡም ያለአግባብ ቆሻሻ ከመጣል በመቆጠቡ አድካሚው የፅዳት ሥራ መቀነሱን ይናገራሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙላት ተገኝ በበኩላቸው፣ ከአምስት ዓመት በፊት አዲስ አበባ አሁን በምትታየው መልኩ አልነበረችም፡፡ ከፍተኛ የፅዳት መጓደል የሚታይባት ከተማ ነበረች፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡ በፅዳት ስራው የነበረው ተሳትፎ ዝቅተኛ የነበረበት፣ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻም ለመልሶ መጠቀም የሚውለውም እዚህ ግባ የሚባል እንዳልነበረ ያነሳሉ፡፡

እነዚህ ችግሮች እያሉ ከተማዋን ፅዱ ማድረግ ስለማይቻልም፤ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እና ለመልሶ መጠቀም የሚውለውን ደረቅ ቆሻሻ ለማሳደግ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ፅዳትን ባህል ማድረግ ግንዛቤ ከመፍጠር እንደሚጀምር የሚያነሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሙላት፣ ከዚህ አኳያ ተቋሙ ከማዕከል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር "የግንዛቤና የህብረተሰብ ተሳትፎ" በሚል መዋቅርና አደረጃጀት በመፍጠርና ተገቢውን ባለሙያ በመመደብ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

ፎቶ- ከገፀ ድር
በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማቶች ውብና ፅዱ ገፅታ የተላበሰው የአራዳ ፓርክ በከፊል

በከተማዋ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች ከ2 ሺህ በላይ የግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያዎች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡ ባለሙያዎቹ ቤት ለቤት በመዞር ማህበረሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲይዝና እንዲለይ በማስተማር ፅዳት ባህል እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር፣ በቡና ጠጡ መድረኮች፣ ሰዎች በብዛት በሚንቀሳቀሱባቸው በዋና ዋና አደባባዮችና መንገዶች ፊት ለፊት እንዲሁም በየሳምንቱ ብሎኩን መሰረት አድርጎ በሚደረጉ የንቅናቄ ስራዎች፣ በየሳምንቱ አርብ በትምህርት ቤቶች የፅዳት ንቅናቄ እና በሌሎች መንገዶች ህብረተሰቡ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አስተዳደር ጋር በተያያዘ ግንዛቤ እንዲኖረው እየተሰራ እንደሚገኝ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሙላት ያስረዳሉ፡፡

ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት በማድረግ፣ የአካባቢ ጥበቃና ንጽህና ክበባት ተቋቁመው በትምህርት ቤት የፅዳት ባህልና አስተሳሰብ ለመፍጠር እየተሰራ ነው፡፡ ልጆችም ከታች ጀምሮ ንጽህናን እያወቁ እየተገበሩ ሲሄዱ ውጤቱም በሂደት እየታየ ይመጣል ይላሉ አቶ ሙላት፡፡

ከማዕከል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር የሕብረተሰብ ተሳትፎን ለማሳደግ ከ2 ሺህ በላይ ባለሙያዎች ቤት ለቤት በመዞር ግንዛቤ እየፈጠሩ ነው። ከኃይማኖት አባቶች ጋር በመተባበርም ቆሻሻን በዘፈቀደ መጣል ከሞራልና ከሕግ አንፃር ተቀባይነት የሌለው ድርጊት መሆኑን በማስተማር ከ629 ሺህ በላይ አባወራዎችንና እማወራዎችን ማሳተፍ ተችሏል።

ሕብረተሰቡን በባህሪ ለመለወጥ እና ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ለማስቀረት የወጣው ደንብ ቁጥር 167/2016 ለዚህ ለውጥ ትልቅ እገዛ አድርጓል። ለአብነትም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ዘያዳ ኑረዲን፣ ከቤታቸው ፊት ለፊት የነበረውን የቆሻሻ ማከማቻ አጽድተው አትክልት በመተከላቸው ቦታው አረንጓዴ፣ ውብና ፅዱ በመሆኑ መደሰታቸውን ነግረውናል። አክለውም "ፅዳት የስልጣኔ ምልክት በመሆኑ፣ የለሙና የፀዱ ስፍራዎች ውበታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ የመዲናዋ ነዋሪዎች ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል" ብለዋል፡፡

ከኤጀንሲው ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው በከተማዋ ከሚመነጨው ቆሻሻ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው የሚበሰብስ እና መልሶ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ነው። ከለውጡ በፊት ይህንን ቆሻሻ ወደ ሀብት በመቀየር ረገድ የነበረው እንቅስቃሴ አነስተኛ የነበረ ቢሆንም፣ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በተዘረጋው አሰራርና ድጎማ ሰፊ ለውጥ መጥቷል።

በአሁኑ ወቅት ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 15 በመቶ የሚሆነው መልሶ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። በቅርብ በጀት ዓመታትም በመልሶ መጠቀም የተደራጁ ማህበራት ከ3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አግኝተዋል። የሚጣልና የሚቃጠል የነበረውን ቆሻሻ ወደ ሀብት መቀየር መቻሉ የትልቅ ባህል ለውጥ ማሳያ ነው።

በሌላ በኩል አዲስ አበባ 7 ትላልቅና ከ76 በላይ ትንንሽ ወንዞችን ተፈጥሮ የለገሰቻት ሀብታም ከተማ ናት። ይሁን እንጂ ቀደም ባሉት ዘመናት ወንዞች የወንጀለኞች መሸሸጊያና የቆሻሻ መጣያ ነበሩ። አሁን ግን በኮሪደርና በወንዝ ዳርቻ ልማቶች እንደ አዲስ ተወልደዋል፡፡ ውብ፣ ፅዱና ተናፋቂ ሆነው ወደ መዝናኛ ስፍራነት ተቀይረዋል። ለአብነትም የካቲት 30 ቀን 2018 ዓመተ ምህረት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በድል ፕላዛ እና የቁርጡሚ የወንዝ ዳርቻ ልማት ምረቃ ላይ "በአንድ ወቅት የቆሻሻ መጣያ የነበረውን ስፍራ ዛሬ ውብ፣ ለዐይን ማራኪ እና የከተማዋ የቱሪስት መስህብ አድርገን ገንብተነዋል" ማለታቸው አይዘነጋም፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጤና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሰይድ ትኩ፣ "ጽዱ ጎዳና ኑሮ በጤና" የተሰኘው ንቅናቄና በኮሪደር ልማቱ እየታዩ ያሉ ለውጦች ማህበረሰቡን ከጤና ችግሮች ለመጠበቅ ወሳኝ መሆናቸውን ገልጸዋል። ፕሮፌሰሩ አክለውም፣ ባልታከመ ውሃና ቆሻሻ ቦታዎች የሚያድጉ አትክልቶች (እንደ ቲማቲም፣ ቆስጣና ጎመን ያሉ) በሽታ አምጭ ህዋሳት እንደሚገኙባቸው በጥናት ማረጋገጣቸውን በመግለጽ፣ የተቀናጀ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ለአካባቢና ማህበረሰብ ጤና ወሳኝ መሆኑን አስምረውበታል።

እንደ ኪጋሊ፣ ሲንጋፖር እና ጃፓን ያሉ ዓለም አቀፍ አርአያ ከተሞች ወንዞቻቸውን በመጠበቅና አካባቢያቸውን ፅዱ በማድረጋቸው ነዋሪዎቻቸው ከፍተኛ የጤናና የስነ-ልቦና እፎይታ አግኝተዋል። የእነዚህ ከተሞች ተሞክሮ እንደሚያሳየው የወንዞችና የጎዳናዎች ማበብ የከተሞችን ውበት ከማሳደጉ ባሻገር የህዝብን ምርታማነት ያጎለብታል።

ይህን የልማት፣ ፅዳትና ውበት እንቅስቃሴ ዘላቂ ለማድረግ የመንግስት፣ የሚዲያዎች እና የህብረተሰብ አንቂዎች የተቀናጀ ጥረት ወሳኝ ነው። መንግስት ህግን ከማስከበር ጎን ለጎን የግንዛቤ ፈጠራውን በማስፋፋት፣ ሚዲያዎች፣ የኃይማኖት አባቶችና አንቂዎች ደግሞ የፅዳት ባህልን የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ መልዕክቶችን በማስተላለፍ አርአያ ሊሆኑ ይገባል።

በመሆኑም በአዲስ አበባ እየተከናወነ ያለው የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የቆሻሻ አወጋገድ ዘመናዊ አሰራር እና የወንዝ ዳርቻዎች ልማት የከተማዋን የክትመት ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ያማሩና ለጤና ምቹ የሆኑ ልማቶችን መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት በመሆኑ ህብረተሰቡ እያደረገ ያለውን ንቁ ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ለንግዱ ማህበረሰብ ዘመናዊ አገልግሎት ለማቅረብ ምን እየተሰራ ነው?

በደረጀ ታደሰ

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ መስከረም 20 ቀን 2019 ዓ.ም. በተካሄደው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የከተማ አስተዳደር መንግሥት ምስረታና 4ኛ ዙር የመክፈቻ ጉባዔ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መዘርዘራቸው ይታወሳል፡፡ ከእነዚህ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል፤ “ለንግዱ ማህበረሰብ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት መስጠት” የሚለው ይገኝበታል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግ፤ በተለይ እንደ ከተማ አስተዳደር የንግድ እንቅስቃሴ ሕጋዊ ሥርዓቱን እንዲጠብቅ፣ ለንግድ ማህበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ እና ዘመናዊ እንዲሆን...፤ “ከዚህ ቀደም ምን ተሠራ፣ በቀጣይስ ምን ለመሥራት ታቅዷል?” የሚሉ ጥያቄዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅን ጠይቀናል፡፡

ፎቶ፦ ከፋይል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ

“ቢሮው ባለፉት ዓመታት ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና ቀልጣፋ የንግድ ስርዓትን በመዘርጋትና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ ዘርፈ-ብዙ ተግባራት አከናውኗል፤ በማከናወን ላይም ይገኛል” ያሉት ወይዘሮ ሀቢባ፤ በተሠሩት ሥራዎች የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለመሻሻሉ የንግዱ ማህበረሰብ እና ነዋሪው ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ ለዚህ አበረታች ለውጥ መምጣት ባለፉት ዓመታት ተቋማዊ አሠራርን በማሻሻል፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ በማዋል፣ አዳዲስ እና ወቅቱን የዋጁ ሕጎች በአዲስ ወጥተው እንዲሁም በነባሮቹ ላይ ማሻሻያዎች ተደርገው በሥራ ላይ በማዋል ረገድ የተተገበሩ ወሳኝ እርምጃዎች ቁልፍ አስተዋፆኦ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

በንግድ ቢሮ የሚሰጡ አገልግሎቶች በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ረገድ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት አበረታች ውጤት የተመዘገበ መሆኑን የጠቆሙት የቢሮው ኃላፊ፤ በተሠራው ሥራ እንደ ቢሮ ዘጠኝ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶች ለአገልግሎት በቅተዋል። ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል ተገልጋዮች በአካል ወደ ቢሮ ሳይመጡ የንግድ ፈቃድ በኦንላይን ማውጣት፣ ማደስ፣ ማሻሻል እና መሰረዝ የሚያስችለው (የኦንላይን የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ ስርዓት - eTrade Portal)፣ የንግድ ተቆጣጣሪዎችና ባለሙያዎች መስክ ላይ በመውጣት የንግድ ተቋማትን በሚጎበኙበት ወቅት የንግድ ፍቃድ ህጋዊነትን፣ የደረጃ መሟላትንና የግብር ታማኝነትን በዲጂታል መንገድ ለመቆጣጠር ያስቻለው የቤት ለቤት (Door-to-Door / Field Inspection) የንግድ ፍቃድ ቁጥጥር እና ኦዲት ሲስተም)፣ መደበኛ ያልሆኑ ነጋዴዎች ሲስተም፣ የገበያ ዋጋ መረጃ ማሳያ ሲስተም፣ የቅሬታ እርካታና ጥቆማ ሲስተም፣ የአመራሩና የቁጥጥር ባለሙያ የመታወቂያ ህጋዊነት ማረጋገጫ ሲስተም፣ ስማርት ኦፊስ ሲስተም፣ የንብረት አስተዳደር እና EGP እንደሚገኙበት ተናግረዋል፡፡

እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ፍትሐዊና ከብልሹ አሠራር የተጠበቀ ለማድረግ አስተዋፅዖዋቸው ጉልህ እንደሆነ የገለጹት ወይዘሮ ሃቢባ፣ በቴክኖሎጂ የመጠቀም ልምዱም እያደገ መጥቷል፣ ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት ጊዜ (መስከረም መጨረሻ/2019 ዓ.ም.) ድረስ ከ828 ሺህ በላይ ደንበኞች ተገልግለዋል። አገልግሎቶቹ በቴክኖሎጂ ተደግፈው መሰጠታቸው የደንበኞች እርካታ ከፍ እንዲል፣ በተቋሙ ያላቸው አመኔታ እንዲሻሻል፣ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲቃለል እንዲሁም የንግድ ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ተልዕኮ ውጤት እንዲያመጣ እገዛ ማድረጉን አንስተዋል፡፡

አዲስ አበባ በፍጥነት እያደጉና እየዘመኑ ካሉ የዓለም ከተሞች አንዷ ነች፡፡ በዚች ከተማ የሚከናወነው የንግድ እንቅስቃሴ በጣም ከፍተኛ የሚባል ነው፡፡ ይህን የንግድ እንቅስቃሴ ሕግና ሥርዓቱን የጠበቀ፣ ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና ቀልጣፋ ለማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ዘመኑን በዋጁ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶች ታግዞ ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በአገልግሎት ላይ ያሉ ሕጎችን ማሻሻል፣ አዳዲሶችን ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር በቢሮው የተሠሩ ሥራዎች በአዎንታዊነት የሚጠቀሱ ስለመሆናቸው ኃላፊዋ ገልጸዋል፡፡

> **አገልግሎቶቹ በቴክኖሎጂ ተደግፈው መሰጠታቸው የደንበኞች እርካታ ከፍ እንዲል፣ በተቋሙ ያላቸው አመኔታ እንዲሻሻል፣ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲቃለል እንዲሁም የንግድ ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ተልዕኮ ውጤት እንዲያመጣ እገዛ አድርጓል**

ወይዘሮ ሀቢባ እንዳብራሩት፤ የሕግ ማሻሻያ ከተደረገባቸው መካከል “የንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008” አንዱ ሲሆን፤ አዋጁ “በንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 1150/2011” ማሻሻያ ተደርጎበታል። ማሻሻያው የተወሰኑ አንቀጾችና ንዑስ አንቀጾች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ተደራሽ ለማድረግ አስችሏል፡፡ በተጨማሪም መዲናዋ ለአዳዲስ የንግድ ስራዎች መጀመር ምቹነቷን እና ተመራጭነቷን አሳድጓል፡፡

መደበኛ ያልሆነ ንግድ ስራን ለመምራትና ስርዓት ለማስያዝ የተሻሻለ እንዲሁም በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ በአዲስ የወጣ ሕግ (ደንብ) ስለመኖሩ ኃላፊዋ ጠቅሰዋል፡፡ በማብራሪያቸው እንደገለጹት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ ንግድ ስራን ለመምራትና ስርዓት ለማስያዝ በማስፈለጉ ከዚህ ቀደም የነበረው ደንብ ቁጥር 88/2009 በደንብ 184/2017 ተሻሽሎ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይህ መሆኑ፤ በከተማዋ ተስፋፍቶ የነበረው መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥርዓት እንዲይዝ አድርጓል፡፡ በከተማዋ የትራፊክ ፍሰት እና እንቅስቃሴ፣ ውበት ገጽታ እና ጽዳት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ተቀርፏል፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት፣ በከተማዋ ሰላም እና ጸጥታ አጠባበቅ ላይ ይፈጥር የነበረው ጫና ቀንሷል፡፡

የከተማዋን ፈጣን ዕድገትና ዘመናዊነት እንዲሁም ዓለም አቀፋዊነት ታሳቢ በማድረግ፤ የማታንቀላፋ ከተማነቷን ከሚያረጋግጡ እንቅስቃሴዎች አንዱ 24/7 (ሰባቱንም ቀናት ሃያ አራት ሰዓት) ያልተቋረጠ የንግድ እና የትራንስፖርት እንቅስቃሴ መኖር ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ “ደንብ ቁጥር 185/2017” ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይህ ሕግ (ደንብ) በመተግበሩ የመጣውን ውጤት በተመለከተ ኃላፊዋ ሲያብራሩ፤ “ኢኮኖሚን ለማሳደግ አግዟል፡፡ የምሽት የስራ ባህልን አሻሽሏል፡፡ ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድልና ገቢ ፈጥሯል፡፡ የከተማውን ውበት እና ጽዳት አሳድጓል። ለንግዱ ማህበረሰብ እና ለሸማቹ ምቹና ቀጣይነት ያለው የንግድ አሰራርን መዘርጋት ተችሏል፡፡” ብለዋል፡፡

በመዲናዋ ጤናማ፣ ፍትሐዊ እና ዘመናዊ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ብሎም እንዲሰፍን ባለፉት ዓመታት በቢሮው አማካኝነት በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን የቢሮው ኃላፊ ገልጸዋል። ይህ ሥራ በዋናነት በንግድ ሥራ ላይ ባሉ ተቋማትና ድርጅቶች ላይ በሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር መፈጸም ነው። በተሠራው ሥራም የንግድ ሥርዓቱን ለማወክ፣ የኑሮ ውድነትን ለማባባስ ሕገ ወጥ ተግባራትን የሚፈጽሙትን በመለየት አስተማሪ የእርምት እርምጃ ተወስዷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ2018 በጀት ዓመት ብቻ ያልተገባ ጥቅምን በመፈለግ የኑሮ ውድነትን የሚያባብሱ መሆን አለመሆናቸውን ለመከታተል በ223 ሺህ 760 የንግድ ድርጅቶች የበር ለበር ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ 24 ሺህ 568 ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል። እንደ ጥፋታቸው ዓይነትና ክብደት ህጋዊና አስተዳደራዊ የእርምት እርምጃ በመውሰድ 20 ሺህ 617ቱ ወደ ህጋዊው መስመር እንዲመለሱ ተደርጓል።

በተጨማሪም፤ በተጠቀሰው በጀት ዓመት ለ48 ሺህ 280 የንግድ ድርጅቶች የልኬት መሳሪያዎች ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ስቲከር ተለጥፏል፡፡ 2 ሺህ 353 የልኬት መሳሪያዎችን ወደ ዲጂታል የማሸጋገር ስራ ተሰርቷል፡፡ 349 ሺህ 682 የንግድ ምዝገባና ፍቃድ ማህደሮችን ኦዲት በማድረግ መስተካከል ያለባቸው ጉድለቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲስተካከሉ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም

ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር የመግፋት ሴራ



ግራፊክስ፦ ከገፀ ድር
ኢትዮጵያ የምትገኝበት ስልታዊ ጠቀሜታ ያለው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ

በአሌክስ ብርሀኑ (የሰላምና ደህንነት መምህር እና ተመራማሪ)

ኢሜል፡- alexbirhanu81@gmail .com

የአፍሪካ ቀንድ የዛሬን የጂኦፖለቲካ እውነታ ለመረዳት የኤርትራን ሚና ከኢትዮጵያ የታሪክ ግንኙነት ጋር ብቻ ማብራራት አይቻልም። የኤርትራ ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ፣ የቀይ ባሕር ጂኦፖለቲክስ፣ የግብፅ የዓባይ ውሃ ደኅንነት ስሌት እና ኢትዮጵያን በውስጣዊ ችግሮች ለማስጠመድ የተደረጉ የረጅም ጊዜ ጥረቶች አንድ ላይ ሲታዩ፣ እውነታው ግልጽ ይሆናል፤ ኤርትራ በክልሉ የራሷን ኃይል ለማሳየት ብቻ የተቋቋመች ማዕከል አይደለችም፤ ኢትዮጵያን ለመግታት በተዘረጋ ሰፊ የጂኦፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ወሳኝ ስፍራ የያዘች መድረክ ናት።

ይህ ስርዓት የተመሠረተው ኢትዮጵያ የክልሉ ትልቁ የሕዝብ፣ የገበያ፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ኃይል ሆና እንዳትወጣ በማድረግ ላይ ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ የልማት አቅሟን እንዳታሳድግ፣ የኢነርጂ አቅሟን እንዳታሰፋ፣ በቀይ ባሕር ላይ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ተደራሽነቷን እንዳትመልስ እና በአፍሪካ ቀንድ ያላትን ተጽዕኖ እንዳታጠናክር ማድረግ የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ ነው።

የኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካም ከዚህ ስሌት ተነጥሎ አይታይም። ለዓመታት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ከኤርትራ ግዛት የድጋፍ፣ የስልጠና፣ የማስተባበር እና የሎጂስቲክስ ድጋፍ አግኝተዋል። ይህ የተከተለው አንድ ግልጽ ስሌት ነበረው፤ ኢትዮጵያ ውስጣዊ ግጭት ውስጥ ተይዛ እስከቆየች ድረስ የረጅም ጊዜ ብሔራዊ ግቦቿን ለማሳካት የሚያስችላትን ኃይል ማሰባሰብ አትችልም።

ይህ የማገድ ስትራቴጂ በአንድ ቀን የተፈጠረ አይደለም። ረጅም የጂኦፖለቲካ ታሪክ አለው። የዓባይ ውሃን በሚመለከት የግብፅ ስትራቴጂያዊ ስጋት እና ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ተደራሽነቷን እንዳትመልስ የተደረገው ጥረት በተለያዩ ወቅቶች ተገናኝተዋል። ስለዚህ ዛሬ የሚታየው የሚዲያ ዘመቻ፣ የፖለቲካ ጫና እና የክልላዊ አሰላለፍ አዲስ ክስተት ሳይሆን የቆየ ስትራቴጂ ቀጣይ ምዕራፍ ነው።

ይሁን እንጂ የዚህ ስትራቴጂ ትልቁ ድክመት የታሰበውን ዘላቂ ውጤት ማምጣት አለመቻሉ ነው። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አንድ ግልጽ ትምህርት ያስተምራል፤ የውጭ ኃይሎች የማገድ ስትራቴጂ የሚሳካው በኢትዮጵያ ውስጥ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም በረጅም ጊዜ እይታ ማየት የማይችል፣ የታሪካዊ ኃላፊነት ስሜት የጎደለው እና ለሀገራዊ ጥቅም የፖለቲካ ቁርጠኝነት የሌለው አመራር ሲኖር ብቻ ነው።

በዚህ አውድ የህወሓት የፖለቲካ አቅጣጫ፣ በተለይም በመለስ ዜናዊ ዘመን የተጠናከረው አስተሳሰብ፣ የኢትዮጵያን ረጅም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ጥቅም በአጭር ጊዜ የሥርዓት ደኅንነት ስሌት በመተካት ለዚህ የማገድ ፕሮጀክት ታሪካዊ እድል ፈጥሯል። በወቅቱ የቀይ ባሕር ጥያቄ እንደ የትውልድ ተሻጋሪ ብሔራዊ ጥቅም ከመታየት ይልቅ በወቅታዊ የሥልጣን ስሌት ውስጥ ተዳክሟል። ይህም ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ለማራቅ የተዘረጋው ፕሮጀክት ጊዜያዊ ስኬት እንዲያገኝ አስችሎታል።

ነገር ግን ጊዜ ተለውጧል። ትውልድ ተለውጧል። የኢትዮጵያም ስትራቴጂያዊ እይታ ተለውጧል። ዛሬ አዲስ ትውልድ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በውስጥ ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በክልላዊ፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን ውስጥ እያየ ነው። ይህ ትውልድ የተፈጠሩ ታሪካዊ ስህተቶችን እንደ ዘላለማዊ እውነታ ለመቀበል አልተዘጋጀም።

> ኢትዮጵያ ለምን ከቀይ ባሕር ተለየች? ይህ የተፈጥሮ እጣ ፈንታ ነውን? ወይስ በፖለቲካዊ ውሳኔዎች የተፈጠረ ታሪካዊ ሁኔታ? የዛሬው ትውልድ መልሱን እየሰጠ ነው፤ የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ጥያቄ የተዘጋ የታሪክ ምዕራፍ አይደለም

የሚጠይቀውም ጥያቄ ግልጽ ነው፤ ኢትዮጵያ ለምን ከቀይ ባሕር ተለየች? ይህ የተፈጥሮ እጣ ፈንታ ነውን? ወይስ በፖለቲካዊ ውሳኔዎች የተፈጠረ ታሪካዊ ሁኔታ? የዛሬው ትውልድ መልሱን እየሰጠ ነው፤ የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ጥያቄ የተዘጋ የታሪክ ምዕራፍ አይደለም።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ይህንን ለውጥ በተግባር አሳይቷል። የውጭ ተቃውሞ በራሱ ወደ ስትራቴጂያዊ ስኬት እንደማይተረጎም ግድቡ በግልጽ አረጋግጧል። የውጭ ጫና የኢትዮጵያን ቁርጠኝነት አልሰበረም፤ ከዚህ ይልቅ በራስ መቻል ላይ ያለውን ቁርጠኝነት አጠናክሯል። የህዳሴ ግድብ በዚህ ረገድ አንድ ትልቅ ትምህርት ሰጥቷል፤ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያን ሊጫኑ ይችላሉ፤ ግን ብሔራዊ ቁርጠኝነት ካለ የኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ ግብ ሊያስቆሙ አይችሉም።

ከዚህ አንጻር የቀይ ባሕር ጉዳይ ቀጣዩ ታሪካዊ ጥያቄ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር ተደራሽነቷን እንደ ቅንጦት ሳይሆን እንደ ረጅም ጊዜ ብሔራዊ ጥቅም ትመለከታለች። ይህ ጥያቄ በጦርነት ብቻ የሚፈታ ጉዳይ አይደለም፤ በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚ፣ በክልላዊ ትብብር፣ በሕጋዊ ማዕቀፍ እና በጠንካራ ብሔራዊ አቅም የሚገነባ ስትራቴጂያዊ ግብ ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያን በውስጣዊ ግጭት ማስጠመድ፣ ከቀይ ባሕር ማራቅ፣ የዓባይ ልማቷን መግታት እና በክልል ያላትን ተጽዕኖ ማሳነስ የሚያስችሉ ዘላቂ የማገድ ስርዓት አይኖርም። የውጭ ኃይሎች ስሌት የኢትዮጵያን እድገት ሊያዘገዩት ይችላሉ፤ ነገር ግን በቁርጠኝነት የሚመራ ብሔራዊ ፕሮጀክትን ለዘላለም ማስቆም አይችልም።

የኤርትራ፣ የግብፅ፣ የህወሓት እና የሌሎች ክልላዊ ተዋናዮች ስትራቴጂያዊ አሰላለፍ ቢቀጥልም፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጉዞ በውጭ ኃይሎች ፍላጎት ብቻ አይወሰንም። የሚወስነው የኢትዮጵያ የራሷ ብሔራዊ ፈቃድ፣ የመንግሥት አቅም፣ የትውልድ ርዕይ እና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ቁርጠኝነት ነው።

ስለዚህ ታሪኩ እዚህ አያበቃም። የውጭ ማገድ ፕሮጀክት ጊዜን ሊያራዝም ይችላል፤ የኢትዮጵያን ስትራቴጂያዊ እጣ ፈንታ ግን ሊወስን አይችልም። የህዳሴ ግድብ የዚህ ማረጋገጫ ነው፤ ቀይ ባሕር ደግሞ ቀጣዩ የታሪክ ጥያቄ ነው።

የቀጠል... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ፡- በለይላ መሀመድ

በመልሶ ማልማት የቤት ተጠቃሚ የሆኑት ወጣት በድሉ አሸናፊ እና ወይዘሮ ጣይቱ አበጋዝ

ወጣት በድሉ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ የነበረውን የህይወት ፈተናም፣ “ወላጅ እናቴ የቀን ገቢ የምታገኘው ከላይ ቆጥ ተሰርቶ አልጋ በማከራየት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ከላይ ቆሻሻ ይንጠባጠብብናል። አልጋ ማከራየቱ ምንም እንኳን የቀን ገቢ ቢያስገኝልንም ለመኖር ግን ምቹ አልነበረም፡፡ ከበሽታውም በዘለለ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጠን ነበር” ሲል ያስታውሳል፡፡

“በቤት ውስጥም ሆነ በሰፈር የግል የሚባል ነገር አለመኖሩ እንደ ወጣት ከባድ ነው” የሚለው በድሉ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ መጸዳጃ ቤትና ማዕድ ቤት በጋራ ይጠቀም ነበር፡፡ በተለይም በርካታ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን መጸዳጃ ቤቶች በወቅቱ ማስመጠጥ አይቻልም ነበር፡፡ ይህ በራሱ ለአካባቢው መቆሸሽ አንዱ ምክንያት ነበር፡፡

በአጠቃላይ አካባቢው የከተማነት ባህሪ አልነበረውም፡፡ አንዱ ቤት ሌላው ላይ ተደግፎ ነው የቆመው፡፡ የመኪና መግቢያ ባለመኖሩ አስክሬን እንኳን ለማውጣት ችግር ነበር፡፡ በቅርቡ በአካባቢው የእሳት አደጋ ተከስቶ የእሳት አደጋ መኪና ለመግባት አመቺ ባለመሆኑ ቤቶች እንደወደሙ ነግሮናል፡፡

በዚሁ ሰፈር ከ40 ዓመት በላይ እንደኖሩ የሚናገሩት ወይዘሮ ጣይቱ አበጋዝም የወጣት በድሉን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡ አሁን እዚህ ህንጻ ቤት ውስጥ ከመግባታችን በፊት አኗኗራችን “በጀመአ” ነበር፡፡ የጋራ ማብሰያ፣ የጋራ መጸዳጃ እንጠቀም ነበር ፡፡

የወይዘሮ ጣይቱ የበኩር ልጅ ወጣት ሀሊማ ኑሩ በበኩሏ የቀድሞ ገጽታውን ያብራራችው፣ “ጽዳቱና ሽታው ለአኗኗር አይመችም፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው የተጨናነቀ የህዝብ አሰፋፈር ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በቂ መጸዳጃ ቤት አልነበረም። በየመንገዱ የሚጸዳዳው ሰው ይበዛል፣ በዚህም ቶሎ ቶሎ በጉንፋን የመያዝ ሁኔታ ይስተዋል ነበር፡፡ ወላጅ እናቴ በአካባቢው መቆሸሽና ሽታ የተነሳ የሳንባ በሽታ ታምማ ከሞት ድናለች” በማለት ነበር፡፡

አካባቢው የተለያዩ ኢ-መደበኛ ንግዶችና በርካታ የሰዎች እንቅስቃሴ ያለበት በመሆኑ ለአካባቢው መቆሸሽ ሌላኛው ምክንያት እንደነበርም አክላለች።

ደስታንም ሀዘንንም ለማሳለፍ አይመችም ነበር፡፡ ማህበራዊ ሕይወታቸው ላይ ያሳድር የነበረውን ጫናም ስትገልጽ፣ “ከአካባቢው መቆሸሽ የተነሳ ጓደኞቼን ይዤ ለመምጣት ያሳፍረኝ ነበር። ከዚህም በላይ ከባዱ ማህበራዊ ችግር እኛ የአካባቢው ወጣቶች ለማግባት ሽማግሌ ለማስላክ ስንፈልግ እንሳቀቅ ነበር፡፡ በሰፈሬ አፍር ነበር” ትላለች፡፡

በመዲናዋ አዲስ አበባ ከተማ ተገንብተው ለዜጎች እየተላለፉ ያሉ ቤቶች የከተሜነት የአኗኗር ዘይቤን ከማሳደግ አንጻር ያላቸውን አበርክቶ አስመልክተን በፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር)ን አነጋግረናቸዋል፡፡

ከተማ ማለት ህንጻ ብቻ አይደለም። ከተማ ማለት ሰው ነው፤ ሰዎች የሚፈጥሩት ግንኙነት ነው። የሚጋሩት ስፍራ ነው። ስለዚህ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪው እንዲጠለልበት ብቻ የሚገነባ ህንጻ ሳይሆን የነገውን ከተሜ ለመገንባት የሚያግዝ የከተማ ልማት መሠረትም ነው

ዳንኤል (ዶ/ር) በማብራሪያቸው፣ እንደ አዲስ አበባ ከባህላዊው አግድም (Horizontal) የነጠላ መኖሪያ ቤት አኗኗር ወደ ሽቅብ (Vertical) የአፓርትመንት እና የጋራ መኖሪያ ቤት (Condominium) አኗኗር መሸጋገር የከተማ ልማት ዘመናዊ መፍትሔ እየሆነ መጥቷል። ይህ ሽግግር ለነዋሪዎች ከሚሰጣቸው ቀጥተኛ ጥቅሞች ባሻገር የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ፣ አስተሳሰብ እና የከተሜነት ባህል በመቅረጽ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይም ውስን የሆነውን የመሬት ሀብት እንዳይባክን ከማድረግ አንጻር ፋይዳው የገዘፈ ነው፡፡ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ ዘመናዊ አፓርትመንቶች እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሬት ብክነትን ከመቀነስ ባሻገር፤ ንጹህና ውብ አካባቢን የሚፈጥሩ እንዲሁም ማህበረሰቡን ወደ ሰለጠነ የከተሜነት አስተሳሰብ የሚያሸጋግሩ የለውጥ ምሰሶዎች ናቸው ብለዋል።

የጋራ መኖሪያ ቤቶች ወይም አፓርትመንቶች ለግለሰቦች ከሚሰጧቸው ጥቅሞች መካከል አስተማማኝ የቤት ባለቤትነት እና ተደራሽነት አንዱ ነው። የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመንገድ፣ የመብራት፣ የውሃ እና የፍሳሽ መሠረተ ልማቶች ተሟልቶላቸው ስለሚገነቡ ለመኖሪያነት በማይመጥንና አመቺ ባልሆኑ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል።

ወጣት በድሉ ያ ሁሉ ችግር አልፎ በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ ኑሮ እየኖረ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ድሮ መጸዳጃ በጋራ ነበር፤ አሁን የግል ነው፡፡ የምግብ ማብሰያ በማህበር ነበር፤ አሁን የግል ነው፡፡ ጭቃ ከነበረው መኖሪያ ቤታቸው ወጥተው በብሎኬት በተሰራ ቤት እየኖሩ ነው፡፡ ድሮ በቤቱና በሰፈሩ ስለሚያፍር ጓደኞቹን ወደ ቤቱ እንዲመጡ አይጋብዝም ነበር፡፡ አሁን ግን ፕሮግራም ቢኖርም ባይኖርም እንዲመጡ ይፈልጋል፡፡ ከቤቱ ምቾት በተጨማሪም የሰፈሩ ገጽታ ተለውጧል። ሰፊ የእግረኛና የመኪና መንገድ ወጥቶለታል፡፡ ወደፊትም ከዚህ የበለጠ እያማረ እንደሚሄድም ያለውን ተስፋ በመግለጽ፣ “አሁን በቤቴም በሰፈሬም አላፍርም፡፡” ሲል ሀሳቡን ደምድሟል፡፡

ወይዘሮ ጣይቱም፣ “በጸዱ እና ምቹ ቤት ውስጥ እየኖርን ነው፡፡ የግል መጸዳጃ እና ማብሰያ ቤት አለን፡፡ ቆሻሻ ሽታ የለም። የሚመጣ እንግዳ ተደስቶ ይሄዳል፤ እኛም ሳንሳቀቅ እንግዳችንን እናስተናግዳለን” ሲሉ የተሰማቸውን ስሜት በደስታ ገልጸዋል፡፡

ወጣት ሀሊማ የሁለቱን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ፣ “አሁን ላይ የሰፈሩ ገጽታም ሆነ የመኖሪያ ቤታችን ፈጽሞ ተለውጧል፡፡ ከዚህ በኋላ ከመጥፎ ሽታ ጋር ተያይዞ የሚመጣ በሽታ አይኖርም። ከእንግዲህ ሳንሳቀቅ እና ደስ ብሎን እንግዶቻችንን እንቀበላለን” ብላለች፡፡

ዳንኤል (ዶ/ር) በሰጡት ሙያዊ ማብራሪያ፣ ልማቱ የነዋሪውን የዕለት ተዕለት ህይወት የሚያቀልሉ እንደ የመኪና ማቆሚያ፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራ፣ አረንጓዴ ፓርኮች እና የንግድ ሱቆች በቅርበት እንዲገኙ ያደርጋሉ። አብዛኞቹ አፓርትመንቶች የመሠረተ ልማት ተደራሽነት ባላቸው አካባቢዎች ስለሚገነቡም ነዋሪዎች ለትራንስፖርት የሚያወጡትን ጊዜ እና ወጪ እንደሚቆጥቡላቸው ገልጸዋል።

የዘመናዊ ከተማ መሠረት

ዳንኤል (ዶ/ር) አያይዘው እንደሚገልጹት፤ የከተማ ዲዛይን ሰውን ይቀርጻል። የሰው አኗኗርም በተመሳሳይ ከተማን ይቀርጻል። ስለዚህ የምንገነባው ቤት የነገውን የከተማ ሕይወት እንደሚወስን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከተማ ማለት ህንጻ ብቻ አይደለም። ከተማ ማለት ሰው ነው፤ ሰዎች የሚፈጥሩት ግንኙነት ነው። የሚጋሩት ስፍራ ነው፡፡ ስለዚህ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪው እንዲጠለልበት ብቻ የሚገነባ ህንጻ ሳይሆን የነገውን ከተሜ ለመገንባት የሚያግዝ የከተማ ልማት መሠረትም ነው።

ከተማ ማለት ምን ማለት ነው? ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ታላቁ እንግሊዛዊ ጸሐፊ ዊሊያም ሼክስፒር “ህዝቡ ነው፤ መሰረተ ልማቱ ነው" ብሎ ነበር የመለሰው። ዘመናዊ ከተማ ብዙ ህንጻዎች ያሏት ብቻ አይደለችም። ህንጻዎቹ ከአስፋልት እና ከእግረኛ መንገድ፣ ከአረንጓዴ ስፍራ፣ ከህዝብ መጓጓዢያና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በተቀናጀ መልኩ የተገነባ ነው ።

በዚህ አኳኋን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከከተማ ፕላን ተነጥለው ሊታዩ አይችሉም። የመኖሪያ ስፍራው ከትምህርት ቤት፣ ከጤና ተቋም፣ ከገበያ ማዕከል፣ ከመጓጓዢያ አገልግሎትና ከመዝናኛ ስፍራዎች ጋር በቅርበት ሲደራጅ ነዋሪው ብዙ ጊዜና ጉልበት ከማጥፋት ይድናል። ዛሬ በአዲስ አበባ የሚስተወለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም። በየአቅጣጫው በሚካሄደው የኮሪደር ልማት፣ የመሃል ከተማ ማደስ እና አዳዲስ ሰፈሮች ግንባታ ምክንያት በከፍተኛ ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል። በተለይም ባለሀብቶች የሚያስገነቧቸው ባለብዙ ወለል አፓርትመንቶች እና የጋራ መኖሪያ ህንጻዎች የከተማዋን ውበት ከመቀየር ባሻገር የነዋሪዎችን የዕለት ተዕለት ህይወት፣ የማህበራዊ ግንኙነት ዘይቤ እና ስነ ልቦናዊ አስተሳሰብ አዲስ ቅርጽ እየሰጡት

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከትውልድ ግንባታ እስከ እናቶች እፎይታ

- አዲስ አበባ ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ ከተማ መሆኗን በተግባር እያሳየች መምጣቷ ተጠቁሟል

በለይላ መሀመድ

የማለዳዋ ፀሐይ ገና ሙሉ በሙሉ ሳትወጣ፣ ወላጆች ሕፃናት ልጆቻቸውን ወደ ማቆያ ማዕከላት ያስገባሉ። ህጻናቱም በማዕከላቱ የለመዱትን ጨዋታ፣ የሞግዚቶች እንክብካቤ እንዲሁም ከእኩዮቻቸው ጋር የሚያሳልፉትን ውብ ጊዜ ከፊት ለፊታቸው የሚጠብቃቸው መሆኑን ለመረዳት በአካባቢዎቹ ማልዶ መገኘት በቂ ነው፡፡ እኛም በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት የህጻናት ማቆያ ማዕከል በተገኘንበት ወቅት፤ ወደ ማዕከሉ በሚያደርጉት ጉዞ የወላጆቻቸውን እጅ ይዘው፣ አልፎ አልፎም ከእጃቸው ተላቅቀው ቀደም ቀደም እያሉ የሚራመዱ ህጻናትን መመልከት ችለናል፡፡

የማዕከሉን ደጃፍ በዚህ መልኩ የሚረግጡት ህጻናት፣ ወደ ውስጥ የሚገቡት በፈገግታና በፈንጠዝያ ነው። እናቶችም ፍጹም በሆነ መተማመን ልጆቻቸውን ለሞግዚቶቹ አስረክበው ወደ ስራቸው ይሰማራሉ። በማዕከሉ ህጻናቱ ልዩ እንክብካቤ ያገኛሉ። ወላጆቻቸው ልጅ አቅፈው ያለስራ እቤት ውስጥ በመቀመጣቸው ምክንያት ከሚፈጠርባቸው ጭንቀት እና ኢኮኖሚያዊ ችግር መውጫ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የእናቶች የኢኮኖሚ ገቢ ሲያድግ ደግሞ፤ ለቤታቸው እና ለልጆቻቸው ማሟላት ያለባቸውን ነገር ለማሟላት አቅም ያገኛሉ፡፡

ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን ያጋሩት የወይዘሮ በቀለች ከበደ ታሪክም የሚያሳየው ይኼንኑ ነው፡፡ ልጃቸውን አቅፈው በቤት ውስጥ ለማሳለፍ ከተገደዱ እናቶች መካከል አንዷ ነበሩ። አሁን ሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር የሞላውን ልጃቸውን ወደ ማዕከሉ አስገብተዋል። ይህን ከማድረጋቸው በፊት እሱን ለመንከባከብ ያለስራ ቤታቸው ለመዋል ተገድደው እንደነበር በመግለጽ የማዕከሉ አገልግሎት መጀመር ትልቅ መፍትሄ ይዞላቸው እንደመጣ አብራርተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ በቀለች ገለጻ፤ ልጃቸው ወደ ማቆያ ማዕከሉ የገባው ገና የአንድ ዓመት ሕፃን እያለ ነበር። ይህ ዕድል እስኪፈጠር ድረስ ባለቤታቸው በሚያገኙት አነስተኛ ገቢ ኑሯቸውን እንዲመሩ ተገድደው ቆይተዋል። በዚህም እንደ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ይቸገሩ፣ ከዚህ አለፍ ሲልም ሕፃኑ በቂ ምግብ ባለማግኘቱ በተደጋጋሚ ይታመም ነበር። ልጃቸውን ወደ ማዕከሉ ካስገቡ በኋላ ግን አስቸጋሪው የኑሮ ሁኔታ ተቀይሯል።

የህጻናት ማቆያን እንደ እናት ቤት የመገልገል ዕድል ያገኙት ወይዘሮዋ፤ ስራ መስራት ጀመሩ። ባለቤታቸውን በኢኮኖሚ ማገዝ ቻሉ፡፡ የልጆቻቸውን የዕለት ፍላጎት የማሟላት አቅምን ፈጠሩ።

ፎቶ፡-ከፋይ
በቀዳማይ ልጅነት መርሃ ግብር በርካታ ህፃናትና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እናቶች ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ

እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ ለወይዘሮ በቀለች የገቢ መጨመር ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በትውልድ ላይ የሚታይ ዘላቂ መሰረትን መገንባትም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ልጃቸው በማዕከሉ በመግባቱ ጤናማ ሆኗል። ከሌሎች ሕፃናት ጋር በመጫወት፣ በመዝሙር እና በተለያየ መንገድ በመማር የንግግር ቋንቋውን ማሳደግ ጨምሮ የተለያዩ ጥቅሞችን ማግኘት ችሏል። ይህን ያመቻቸው መንግስት ሊመሰገን እንደሚገባው አብራርተዋል።

የወጣት ብዙዬ ፍልቀት እና የህጻናት ማቆያ ማዕከሉ መስተጋብርም፤ እናቶች ከማቆያ ማዕከላት በብዙ መልኩ ሊገለጽ የሚችል ጥቅም እያገኙ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እኝህ እናት የእለት እንጀራዋን ለማግኘት የሁለት ዓመት ልጇን አዝላ የተለያዩ የጉልበት ስራዎችን ታከናውን እንደነበር ያሳለፈችውን ጊዜ ከትውስታ ማህደሯ እያወጣች ካጋራችን ሃሳብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ታሪኳን ስትተርክ በሃዘንና በደስታ ተቃርኖ ስሜት ውስጥ እየተመላለሰች ነው፡፡ የብሶቷ ምንጭ ባለቤቷ ከጎኗ ሳይኖር ልጇን ለብቻዋ፣ ያውም በድህነት ያለማንም ደጋፊ ማሳለፍ ነው፡፡ የደስታዋ ምንጭ ደግሞ "አለሁልሽ፣ በወጣትነት አቅምና ጉልበትሽ ሮጠሽ፣ ጥረሽ ግረሽ ኢኮኖሚያዊ ችግርሽን አስወግጂ" የሚል ደጋፊ በማዕከሉ አማካኝነት ማግኘቷ ነው፡፡

"ልጅ አዝሎ ስራ መስራት ከባድ ከመሆኑም ባለፈ ብዙ አሰሪዎች በዚህ መልኩ ሲያዩኝ ሳያሰሩኝ ይመልሱኛል። ይህ ደግሞ ለበርካታ ጊዜያት በችግር ውስጥ እንድኖር አድርጎኛል" የምትለው ወጣት ብዙየ፣ ልጅ አዝሎ፣ እንኳን ስራ መስራት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስም እንደሚከብድ ታነሳለች፡፡ "የግድ መስራት ሲኖርብኝ ልጄን አቧራና ቆሻሻ ባለበት መሬት ላይ አስቀምጠው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለጉንፋንና ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ይጋለጥ ነበር፡፡ ከዚህ አለፍ ያለ አደጋ በልጄ ላይ ይደርሳል በሚል ጭንቀት ውስጥም የምገባበት ጊዜ ነበር። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ስራ መስራት ለእናትና ለልጅ የደህንነት ስጋት ሆኖብኝ ብዙ ጊዜያትን አሳልፌያለሁ፡፡" ስትልም ቀደም ባሉት ጊዜያት፤ አንዳንድ ተባራሪ የጉልበት ስራዎችን ለመስራት ስትል በጣም አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ትወስን እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

አሁን ላይ የወጣት ብዙየ የሕይወት መንገድ በጎ መስመር ይዟል፡፡ ወደ ህጻናት ማቆያ ማዕከሉ ልጇን ካስገባች በኋላ እፎይታ አግኝታለች። ጠዋት አንድ ሰዓት ተኩል ወደ ማዕከሉ አምጥታ ለተንከባካቢ ሞግዚቶች በመስጠት፣ ያለምንም ሀሳብና ጭንቀት ወደ ስራዋ ትሄዳለች። በሥራዋ በቂ ገቢ ታገኛለች። ከነበረችበት ኢኮኖሚያዊ ችግር ራሷን ማላቀቅ ችላለች፡፡ ስለምትበላው ነገር ሳትጨነቅ እንድትኖር አድርጓታል፡፡ የእሷም ሆነ የልጇ ደህንነት ተጠብቋል። ከሌሎች ሕፃናት ጋር እየተጫወተ በመዋሉ ከቀን ወደ ቀን አካላዊ እድገቱ እየተሻሻለ መጥቷል። የማዕከሉ ንጽህናና እንክብካቤ ከራሷ በላይ ለልጇ የተሻለ ዕድል እንደሆነ በመግለጽም ይህን ላመቻቹ አካላት ምስጋና አቅርባለች።

በማዕከሉ በሞግዚትነት የሚያገለግሉት ወይዘሮ የማርውሀ ቢምረው፤ ማዕከሉ ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እያገለገሉ አንድ ዓመት ሆኗቸዋል። ሕፃናትን የመንከባከብ ስራቸውን በፍቅርና በደስታ እያከናወኑ ነው፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ፣ እሳቸውና ባልደረቦቻቸው፤ ልጆቹን ከወላጆቻቸው ከተረከቡ በኋላ ንጽህናቸው እንዲጠበቅ፣ የምግብ ሰዓታቸውን ጠብቀው እንዲመገቡ ያደርጋሉ፡፡ ጸጉራቸውን ያበጥራሉ፤ ይሰራሉ፡፡ በበቂ ሁኔታ እንዲጫወቱና እንዲዝናኑ ያደርጋሉ። በጨዋታ ውስጥም ብዙ ነገር ይማራሉ። ምንጣፍ ማጠፍን፣ ዕቃዎችን በስርዓት ማስቀመጥን እና የተለያዩ ነገሮችን መገጣጠምን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ የሕፃናቱን አስተሳሰብ ችሎታ የማዳበር ስራ ይሰራሉ።

የማዕከሉ የስነ ልቦና ባለሙያ የሆኑት አቶ በረከት ፈንታሁን ማዕከሉ ሕጻናትን የሚቀበልበትንና የሚያቆይበትን አሠራር በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ፤ "ሕፃናቱ ወደ ማዕከሉ ሲገቡ በየእድሜቸው ፋይል ይደረጋል፡፡ በየሁለት ወሩ ከወላጆች ጋር ውይይት በማድረግ ሕፃናቱን እንዴት መያዝና ለእድገታቸው ምን ማድረግ እንደሚገባ ምክር ይሰጣል። በየእድሜያቸው የእድገት ክትትል ይደረጋል፡፡ በየሦስት ወሩ የሕፃናቱ እድገት ይገመገማል። በተለይም የአእምሮ፣ የማህበራዊና ሥነ ልቦና ሁኔታ እንዲሁም አካላዊ እድገት ክትትል ይደረጋል" ብለዋል፡፡

ባለሙያው አክለው እንዳስረዱት፤ ወደ ማዕከሉ ከገቡ ሕጻናት መካከል አብዛኞቹ በቋንቋ ክህሎታቸው እና በአካላዊ እድገታቸው ለውጥ አምጥተዋል፡፡ አንዳንድ ሕፃናት ሲመጡ መናገር አይችሉም ነበር፡፡ በጊዜ ሂደት ግን ቃላትን ማውጣት፣ ከቃላት ወደ ሀረግ መናገር ተሸጋግረዋል፡፡ በቋንቋ ክህሎት ሂደት ውስጥ የሕጻናት ክህሎት ከሀረግ ወደ አረፍተ ነገር እያደገ ይመጣል። ይህንም በማዕከሉ ከገቡ ሕጻናት የለውጥ ግምገማ መረዳት ተችሏል። እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነታቸው እያደገ መጥቷል። ለምሳሌ፡- መጀመሪያ ላይ ሰው ጋር መቅረብ የማይወዱ ልጆች በሂደት አብሮ መብላት መጫወት እየተለማመዱ መጥተዋል፡፡

አቶ አዳነ ገበየሁ የማዕከሉ አስተባባሪ ናቸው፡፡ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጡን መረጃ፤ ማዕከሉ 12 የሕፃናት ተንከባካቢዎች፣ አንድ የጤና እና አንድ የሥነ ልቦና ባለሙያ፣ ሁለት የምግብ ዝግጅት ሠራተኞች፣ አንድ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች

በአብርሃም ገብሬ

ባሳለፍነው ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ይቀርባሉ። ከእነዚህ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የመጽሐፍ ፊርማ ሥነ ስርዓት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

መጻሕፍት

በደራሲ አዳም ረታ ድርሰቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሂሳዊ መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ ባሳለፍነው ሳምንት በይፋ ተመርቆ ለንባብ የበቃው "የጥበብ ቃሊም ሥነ አዳም" የተሰኘው መጽሐፍ፣ በትግስት ሳሙኤል እና በቢኒያም አበራ የተጻፈ ሂስ ቀመስ መጽሐፍ ነው ተብሏል፡፡ ዛሬ ደግሞ በዚሁ በአዲሱ ሂሳዊ መጽሐፍ ላይ የፊርማ ሥነ ስርዓት ይደረጋል፡፡ የፊርማ ሥነ-ሥርዓቱ የተሰናዳው ለገሃር በሚገኘው በአዲሱ የጃዕፈር መጽሐፍ መደብር ውስጥ ነው። ዛሬ ከቀኑ ከ8 ሰዓት ጀምሮ እስከ 10 ሰዓት በመጽሐፉ ላይ የፊርማ ሥነ ስርዓት ይደረጋል፡፡

በወጣቷ ደራሲ ማርታ አሰፋ የተጻፈው "የጭን ስር ቁጭት" መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው፡፡ ደራሲዋ በማህበራዊ የትስስር ገጿ በኩል የመጽሐፉ ቅድመ ሽያጭም እያደረገች ትገኛለች፡፡ መጽሐፉ በቀጣይ ሳምንት ለንባብ እንደሚበቃ የገለጸችው ደራሲዋ፣ የሥነ ጽሑፍ አፍቃሪያን መጽሐፏ በእሷ በኩልና በተለያዩ የመጻሕፍት መደብር እንደሚያገኙትም ጠቁማለች፡፡

"ደንበኞሎጂ" የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ መጽሐፉ ስሜታዊ ብልህነት ለላቀ የደንበኛ አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም በደንበኛ አያያዝ ዙርያ ያተኩራል ተብሏል፡፡ "ብዙዎቻችን ደንበኛን ማገልገል ማለት ጥያቄዎችን መመለስ፣ ችግሮችን መፍታት ወይም መረጃ በመስጠት የሚወሰን ነው ብቻ ብለን እናስባለን። ነገር ግን እውነተኛው አገልግሎት ከተግባር በላይ የሆነ ነገርን ይጠይቃል፤ እርሱም ስሜታዊ ብልህነትን (Emotional Intelligence) ነው። ስሜታዊ ብልህነት ማለት የራሳችንን ስሜት መረዳት እና መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን፣ የደንበኛውን ስሜት ማጤን፣ መለየት፣ መረዳት እና ለእሱ ተገቢውን ምላሽ መስጠት መቻል ነው" የሚል ቅኝት መጽሐፉ እንዳለው ተገልጿል።

ፎቶ :- ከገፀ ድር

ከመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

ስዕል

"አዲስ ቅኝት" የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በይፋ መታየት ሊጀምር ነው። በሰዓሊ ፍቅረአዲስ ላመስግን የተሳሉ የተለያዩ ስዕሎች የሚቀርቡበት አውደ ርዕዩ፣ የፊታችን ረዕቡ ጥቅምት 11 ቀን፣ 2019 ዓ.ም መስቀል አደባባይ በሚገኘው በፈንድቃ ባህል ማዕከል ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በይፋ ይከፈታል፡፡ ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አንስቶ መታየት የሚጀምረው አውደ ርዕዩ እስከ ፊታችን ሰኞ ህዳር 07 ቀን፣ 2019 ዓ.ም ድረስ ይቆያል፡፡ መላው የጥበብ አፍቃሪያን በስፍራው ተገኝታችሁ የስዕል አውደ ርዕዩ ላይ እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡

በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴስ በይፋ የተከፈተው የስዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ ሰዓሊ ሙሉ ለገሰ "I Carry – Je Porte" በሚል ርዕስ በተለያዩ ጊዜያት የሳለቻቸው የሥዕል ሥራዎች የቀረቡበት ይሄ አውደ ርዕይ፣ ከሳምንት በፊት በይፋ ተከፍቶ በመታየት ላይ ነው፡፡ ሰዓሊዋ ረቂቅ የአሳሳል ዘይቤ በመጠቀም የሳለቻቸው የጥበብ ሥራዎች እስከ ፊታችን ጥቅምት 21 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ ለዕይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የጥበብ አፍቃሪያንም በሥፍራው ተገኝታችሁ እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡

የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 "12ቱ እንግዶች" እንዲሁም በ11:30 "በር የሌለው ቤት" ቴአትሮች ይታያሉ። እሁድ ደግሞ በ7፡30 "ንጉስ አርማሕ" እንዲሁም በ11፡30 ደግሞ "እምዬ ብረቷ" ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ "እሳት ወይ አበባ" ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ" ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጐ አካባቢ የሚገኘው የህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "የንባብ ከተማ" የተሰኘው አዲስ የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት "ወህኒ አምባ" ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ደግሞ "አትጥሪኝ" የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11፡00 ሰዓት "አሉ" የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11፡30 "ነገሩ አይቆምም፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት ሰዴታ (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

የቁጥር ጨዋታ

የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በግራ በኩል ወደ ታች በተደረደሩት ሶስት ክቦች ውስጥ ያሉ ቁጥሮች ወደ ጎን እንደረድራለን፡፡ ከዚያ በኋላ የተደረደሩት ቁጥሮች በቀኝ በኩል መሃል ላይ በብቸኛ ቁጥር እናባዛዋለን፡፡ አባዝተን ያገኘነው ውጤት ሶስተኛው መደብ ክብ ላይ ወደ ታች የተደረደሩት ቁጥሮች ጋር መመሳሰል አለበት፡፡ እነዚህ ቁጥሮች ወደ ጎን ደርድረን በስንት ብናባዛቸው ነው በቀኝ በኩል የመጨረሻ ሶስቱ ክቦች ውስጥ ወደ ታች የተደረደሩት ቁጥሮች የሚመጣው የሚለው ነው፤ የጥያቄው ትክክለኛ መልስ፡፡ ለአብነትም የመጀመሪያ ክብ ውስጥ የተደረደሩት ቁጥሮች አሰራር አብረን እንስራው፤ 116 x 3 = 348 ይሆናል፡፡ 348 ደግሞ በስንት ብናባዛው ነው 696 የሚሆነው? በዚህ መሰረት በጥያቄ ምልክቱ ውስጥ መግባት ያለበት 2 ቁጥር ይሆናል፡፡ 348 x 2 = በቀኝ በኩል ወደ ታች የተደረደሩት 696 ይሆናል፡፡ በዚህም የጥያቄው ትክክለኛ መልስ 2 ይሆናል፡፡ 116 x 3 = 348 ከዚያ በኋላ 348 x 2 = 696 ይሆናል፡፡



የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



በጥበብ የተሸመነው ወርሃ ጥቅምት

በአብርሃም ገብሬ

ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ለሰው ልብ የቀረቡና ዘመን ተሻጋሪ የሚያደርጋቸው አንዱ ፍሬ ነገር ውበት ነው፡፡ በዚህም ከያኒያን አምሳለ-ብዙ የውበት መልኮችን በፈጠራ ሥራዎቻቸው ክሱት ለማድረግ ብዙ ይጥራሉ፡፡ በተለይ የሰውን የጋራ መሻትና ትውስታ በውበት መሸመን መቻል ለአንድ ከያኒ ትልቅ ስኬቱ ነው፡፡ በእርግጥ የወል ትውስታና መሻት ማዕከል ያደረገን የውበት ዕይታ በፈጠራ ሥራ ውስጥ መከሰት ለሁሉም ከያኒያን የተሰጠ ተሰጥኦ አይደለም፡፡

ይህን ለማድረግ ከምንም በላይ እንደ ተፈጥሮ ያሉ የውበት መልኮችን በቅጡ ማስተዋል፣ የወቅቶችን መፈራረቅ ከሰዎች ስሜት ጋር አስተሳስሮ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይሄን መፈራረቅ ተከትሎ የተፈጥሮ መልኮች በሰዎች ስሜት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በቃላትና በዜማ ደርዝ ማስያዝ ለአንድ ከያኒ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ይህን መነሻ በማድረግ የጥቅምት ወር ለምን የኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ምንጭ ሆነ? እንዲሁም በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ውስጥ ያለው ቦታስ እንዴት ያለ ነው? የሚለውን በተመለከተ አጭር ዳሰሳ አዘጋጅቷል፡፡

ጥቅምት ለምን የጥበብ ሥራዎች ምንጭ ሆነ?

ታዋቂው አሜሪካዊ ሙዚቀኛና የፊልም ዳይሬክተር ኒል ያንግ “Harvest Moon” የተሰኘ ተወዳጅ ሙዚቃ አለው፡፡ ሙዚቃው በጥቅምት ምሽት የጨረቃን ውበት ለመግለጽ ያዜመው ነው፡፡ ሙዚቀኛው በጥቅምት ወር ምሽት ላይ የምትወጣውን ልዩ ጨረቃ መነሻ በማድረግ፣ የተፈጥሮን ሃያልነት ያሞግሳል፡፡ ውቧ ጨረቃን መነሻ አድርጎ ፍቅርን ከእሸት ጋር አስተሳስሮ በሙዚቃው ይቀኛል፡፡ በኢትዮጵያም ቢሆን ጥቅምት የተፈጥሮ ድንቅ ውበት ጎልቶ የሚታይበት፣ ያበበው እሸት የሚታጨድበት፣ ሰማይ በሐምራዊና በነጭ ቀለማት አጊጦ የሚታይበት ነው።

ገጣሚና ጋዜጠኛ ያለው አዛነው በግጥም መጽሐፍቱ ውስጥ ተፈጥሮን መነሻ ያደረጉ ግጥሞችን አካትቷል። ወርሃ ጥቅምትና ኪነ ጥበብን መነሻ በማድረግ ለዝግጅት ክፍላችን ባጋራን አስተያየት፣ በተለያዩ ሀገራት ጥቅምት የተፈጥሮ መፍካት፣ የጥረትን ውጤት የመቀዳጀት፣ የደስታ እና የሕይወት ቀጣይነት ማሳያ ተደርጎ ይታያል፡፡ በዚህ ምክንያት በሙዚቃ፣ በግጥምና በሥነ ቃል ውስጥ የሕይወት ሽግግርና የተፈጥሮ ሚዛን አስጠባቂ አድርጎ በመተርጎም የተለያዩ ከያኒያን ለዚህ ወር እንደተቀኙ አጫውቶናል፡፡

እንደ ገጣሚ ያለው ገለጻ፣ በተለያዩ የእንግሊዝኛ የሙዚቃ ሥራዎች ውስጥ ወርሃ ጥቅምት፣ የመጨረሻው የውበት ብልጭታ (በጣም ቀዝቃዛ ከሆነ በረዶ በፊት ያለ) እና አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት ወቅት መሆኑን መነሻ በማድረግ ከያኒያን ለፈጠራ ሥራዎቻቸው መነሻ አድርገው ተቀኝተውበታል፡፡ ለአብነትም:- አየርላንዳዊው ሙዚቀኛ ቫን ሞሪሰን “October Song” በተሰኘው ውብ ሙዚቃው ወርሃ ጥቅምት ቀዝቃዛው የአውሮፓውያን ወራት ከመምጣቱ በፊት ያለ ወር መሆኑን በማውሳት፣ ወቅቱ ሰዎች ወደ ውስጥ እንዲመለከቱና እንዲረጋጉ እንደሚያደርግ በውብ ድምጹ አዚሞለታል፡፡ በዚህም ጥቅምት ከአበባ ወደ ፍሬ፣ ከሙቀት ወደ ለስላሳ ቅዝቃዜ፣ ከውጪ እንቅስቃሴ ወደ ራስ የመመልከቻ ወር ሆኖ እንደ አብነት ይታያል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ የአዲስ ተስፋ፣ የውበትና የደስታ ምልክት ሆኖ በተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ውስጥ ተገልጧል፡፡ ከዚህ አንጻር በጥበብ አፍቃሪያን እና በከያኒያን ዘንድ ልዩ ሥፍራ ይይዛል፡፡ የተፈጥሮን ምስጢርና የሰው ልጅን የስሜት ውጣ ውረድ በውበት፣ በቅዝቃዜና በእሸት ምስል የሚገልጡበት ዘመን ተሻጋሪ የጥበብ ምንጭ የሆነ ወር መሆኑን ገጣሚ ያለው ተናግሯል፡፡


ፎቶ:- ከገጸ ድር
ጥቅምትን በኪነ ጥበብ ከሸመኑት መካከል ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን እና ድምጻዊ ነዋይ ደበበ ተጠቃሽ ናቸው

ሀገራችን ኢትዮጵያም፣ የ13 ወር ጸጋ ባለቤት እንደመሆኗ መጠን የክረምቱ ወቅት አልፎ፣ ደመናው ተገፍፎ መስከረም ሲመጣ ሕይወት ልዩ መልክና ገጽታ ይላበሳል፡፡ በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ወር አደይ አበባ ከሁሉም ቀድማ ብቅ ትላለች። ምድር በአረንጓዴ ቀለም ትዋባለች፡፡ መስኮች በአረንጓዴ ሳር፣ በልዩ ልዩ አበቦች ታጌጣለች፡፡ ወርሃ መስከረምን ሸኝቶ የሚመጣው ጥቅምት ወር ተከትሎ ቀስ በቀስ የደፈረሱ ወንዞች ንጹህ ይሆናሉ፡፡ በመስከረም የጀመረው ልምላሜ እና አበባ በጥቅምት ልዩ ገጽታ ይላበሳል፡፡ አበቦች ሙሉ በሙሉ ያብባሉ፡፡ ቡቃያው ወደ እሸት ይቀየራል። የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች ልዩ ማዓዛ እና ውበት ይላበሳሉ፡፡

ይሄ የተፈጥሮ ውበት ለአንድ ከያኒ ትልቅ የፈጠራ ምንጭ መሆኑን ያጫወተን ገጣሚ ያለው፣ የሰው ስሜት መለዋወጥ ከተፈጥሮ መፈራረቅ ጋር በአንድም ሆነ በሌላ ይያያዛል፡፡ በጣም ቅዝቃዜ የሚበዛበት ወር ላይ የሰው ስሜትና የአኗኗር ዘይቤ አብሮ ይለወጣል፡፡ በቅዝቃዜው ወይም በክረምቱ ምክንያት የሰው እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃ ይገደባል፡፡ በዚህ ምክንያት ወደሚወዱት ሰው ወይም ስፍራ በፈለጉት ጊዜ መጓዝ አይኖርም፡፡ ይሄ ውስንነት የጥበብ ሥራዎች መነሻ በመሆን ስለናፍቆት ይከየናል፡፡ ስለትዝታ ይዜማል። ስለአብሮነት ይወሳል፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ የወቅቶች መፈራረቅ በሰው ላይ የሚያመጣው የስሜትና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ መሆኑን ተናግሯል፡፡

በአንጻሩ ወርሃ ጥቅምት የውበትና የተስፋ መነሻ ነው፡፡ ውበት ደግሞ ስሜትን ያነቃቃል፡፡ ልብን ደስ ያሰኛል። ለአዲስ ተስፋ መነሻ ይሆናል፡፡ ወርሃ ጥቅምት ደግሞ ተፈጥሮ የሚያዳላለት ወር በመሆኑ ለከያኒያን ለፈጠራ ሥራዎቻቸው መነሻ መሆን ችሏል፡፡ ለዚህ ይመስላል አንዳንድ የሀገራችን ከያኒያን ወርሃ ጥቅምትን ዘመን ተሻጋሪ ያደረገ የጥበብ ሥራ የሰጡን፡፡

የጥቅምት አበባ ነሽ አሉ

ከሀገራችን ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ወርሃ ጥቅምትን ህያው ካደረጉ ሥራዎች መካከል ዋነኛው የሙዚቀኛ ነዋይ ደበበ “የጥቅምት አበባ” የተሰኘ ሙዚቃን የሚስተካከለው የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በሀገራችን ለፍቅር፣ ለሃገር፣ ለቤተሰብና ለናፍቆት በርካታ ሙዚቃዎች ተሰርተዋል፡፡ ስለ መስከረም ወር እና አዲስ ዓመትም እጅግ በርካታ ሙዚቃዎች ተቀንቅነዋል። ስለጥቅምት ወር እና አበባ ከተሰሩ ሙዚቃዎች ውስጥ ደግሞ “የጥቅምት አበባ” የተሰኘው ሙዚቃ በውበትና በግጥሙ ወርሃ ጥቅምትን ዘመን አይሽሬ ማድረግ ችሏል፡፡

“የጥቅምት አበባ፤ የጥቅምት አበባ፤
የጥቅምት አበባ ነሽ አሉ፤
አወድሸው አካሌን በሙሉ።
የጥቅምት አበባ፤ የጥቅምት አበባ፤
የጥቅምት አበባ ለሽታ
ለኔ ግን ጣልሽብኝ ትዝታ…”

እያለ የጥቅምት አበባ ማዓዛው የማይረሳ እና ሁልጊዜም ሲታወስ የሚኖር፣ የፍቅር ትዝታም እንደዛው መሆኑን ያቀነቅናል። ጥቅምት ከአበባ ጋር ተሳስራ፣ ከውበት ጋር ተጋብታ በዚህ ሙዚቃ ብቅ ትላለች። ወርሃ ጥቅምት በተለይ በወይና ደጋ እና ደጋማ አካባቢዎች በርካታ አበቦች የሚፈኩበት ጊዜ በመሆኑ ማር የሚቆረጥበት፣ ማሩም ከተለያዩ አበባዎች የሚቀሰም ስለሚሆን ለጤንነት ሁነኛ ነው ተብሎ የሚታመንበት ጊዜም ጭምር ነው።

ድምጻዊ ነዋይ ደበበ ናፍቆቱን በዜማ ያንጎራጎረላት ልጃገረድ እንደ ጥቅምት አበባ፣ መላ አካልን የምታውድ፣ መንፈስን የምታዳርስ ከመሆኗ የተነሳ እንደ ቢራቢሮ እና እንደ ንብ ክንፍ አውጥተው ቢበሩ የማታስቆጭ መሆኗን በዘፈኑ አንስቷል። ከፍቅሩ ጋር ጠጋ ብሎ ለመወያየት ማረፊያ መፈለጉንም አይሸሽግም፡፡

“…ማረፊያ አለ ወይ ፍቅርዬ
እንዳዋይሽ ሚስጥር ጠጋ ብዬ
የጥቅምት አበባ ነሽ
አካል ሰው ነይ ናፈኩሽ
ውበት መዓዛሽ ለሽታ
ፍኪልኝ ልቤ ያግኝ ደስታ…”

በማለትም ጥቅምትና አበባን፣ እንዲሁም ፍቅርን በማዋሃድ በጥቅምት ወር ብቻም ሳይሆን በየትኛውም ወር እና ዘመን ተደማጭና ተወዳጅ ሙዚቃን አበርክቷል፡፡

ድምጻዊው ፍቅርና የጥቅምት አበባን፣ አንዱ ተወዶ አንዱን መጥላት እንደማይቻል፣ ተፈጥሮም በሃሴት፣ ተፈቃሪዋ ልጃገረድም በውበት የተሞላች መሆኗን በዘፈኑ አንጸባርቋል፡፡

በኢትዮጵያ ስለወራት በርካታ ሥነ ቃልና ግጥሞች አሉ፡፡ ጥቅምትን የተመለከቱ በርካታ ግጥሞች ተገጥመዋል፤ ሥነ ቃሎች ተነግረዋል፤ ዘፈኖችም ተሰርተዋል፡፡ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን “ኣቴቴ ዱብራ ኦሮሞ” በተሰኘው ግጥሙ የጥቅምትን ወር ውበት፣ ናፍቆትና እሸት እጅግ ድንቅ በሆኑ ቃላትና ስንኞች ገልጾታል፡፡

ጥቅምት የውበትና የተስፋ መነሻ ነው። ውበት ደግሞ ስሜትን ያነቃቃል። ልብን ደስ ያሰኛል። ለአዲስ ተስፋ መነሻ ይሆናል። ወርሃ ጥቅምት ደግሞ ተፈጥሮ የሚያዳላለት ወር በመሆኑ ለከያኒያን ለፈጠራ ሥራዎቻቸው መነሻ መሆን ችሏል

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክፍለ ከተማ በወረዳ 7 ስር የሚገኘው የሜ/ጀ/ኃየሎም አርአያ የመጀ/ደ/ት/ቤት ለ2018 ዓ/ም የበጀት ዓመት የጨረታው መለያ ቁጥር 001

ሎት 1. አላቂ የፅህፈት መሳሪያዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን......................	2,000
ሎት 2. አላቂ የትምህርት እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን......................	2,000
ሎት 3. የሰራተኞች የደንብ ልብሶች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን..................	2,500
ሎት 4. አላቂ የፅዳት እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን............................	2,000
ሎት 5. ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን.........................	3,000
ሎት 6. ቋሚ የቢሮ እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን..............................	3,000
ሎት 8. ለህትመት ስራዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብርመጠን..................................	2,000
ሎት 9. የተለያዩ መጻሕፍት የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን................................	2,000

በዚህ መሰረት በጨረታ መሳተፍ የምትፈልጉ

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላችሁ፤ የዘመኑን ግብር አጠናቃችሁ የከፈላችሁ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ የተመዘገቡ፤ የቫትና የቲን ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የምትችሉ፡፡
2. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ (CPO) ከጨረታው ሰነድ ጋር ማቅረብ የምትችሉ
3. ለጨረታ ሰነድ ለእያንዳንዱ የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል ይህ ጨረታ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በሜ/ጀ/ ኃየሎም አርአያ የመጀ/ደ/ት/ቤት ፋይናንስ ግዥና ን/አስ/ደጋፊ የስራ ሂደት በግንባር በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የምትጫረቱትን እቃዎች ሳምፕል የሚቀርብባቸው ለሎት1 ለሎት2 ለሎት3 ለሎት 4 ለሎት5 ለሎት8 ለሎት9 ለሎቶቹ ናሙናውን ጨረታው ከመከፈቱ አንድ ቀን በፊት ሳንፕል በሚቀርብባቸው ሎቶች ላይ ያላቀረቡ ለጨረታ ውድድር አይቀርብም ማቅረብ (ማስገባት) አለባቸው ጨረታው ከተከፈተ በኃላ በጨረታ የማናሳትፍ መሆኑን አንገልፃለን፡፡
5. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ስርዝ ድልዝ የሆነ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
7. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሱ /ባሸናፊው/ ትራንስፖርት ከነጉልበት ክፍያው ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት ድረስ ማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
8. ተጫራቾች የምታቀርቡትን ዋጋ ዝርዝር በሰነዱ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ ላይ በግልፅ ሞልታችሁ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ዋናውንና ኮፒ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ በስራ ሰዓት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን በሜ/ጄ/ኃየሎም አርአያ የመጀ/ደ/ት/ቤት ፋይናንስ ግዥና ን/አስ/ደጋፊ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 2 ማስገባት ይኖርባችኋል፡፡
9. የጨረታ ሳጥኑ ማስታወቂያው ከወጣበት በ10ኛው ቀን በ8፡00 ሰዓት ታሽጎ በእለቱ 8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሜ/ጀ/ኃየሎም አርአያ የመጀ/ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 5 ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡ 10ኛው ቀን የበዓል ቀን ወይም የእረፍት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡
10. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፡- በእስፔስፍኬሽን እና በዋጋ ማቅረቢያ ውጭ ሁለት ዋጋ መሙላት አይቻልም እንዲሁም በራስ በተሰጠው ሎት ፎርም ውጭ በእስክርቢቶ መሙላት እና ከታች አማራጭ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፡፡

አድራሻ፡- ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አጠገብ ኖክ ማደያ ጎላ ሚካኤል በሚወስደው መንገድ ገባ ብሎ

ስልክ ቁጥር፡- 011515-40-84 ወይም 096652-10-10 ፖስታ ሳጥን ቁጥር፡- 25993/1000

በል/ክ/ከ/አስ/ወረዳ 7 ት/ጽ/ቤት የሜ/ጀ/ኃየሎም አርአያ የመጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

1. የስፖርት ትጥቅና ቁሳቁስ ግዢ

ስለሆነም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች ቀርበው መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች አግባብነት ያለው በዘመኑ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ፍቃድ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ጨረታ ላይ መሳተፍ እንዲችሉ የተሰጠ ክሊራንስ ማስረጃ፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ የተመዘገቡ ለመሆናቸው የተጫራቾችን የምስክር ወረቀትና የግብር ከፋይነት መለያ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለባቸው፡፡ እንዲሁም የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና ስርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታ ከመከፈቱ በፊት የዕቃውን ስፔስፊኬሽን /ዝርዝር መግለጫ/ ከሚያቀርቡት ዋጋ ጋር አያይዘው ስፖርት ጽ/ቤት ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ጠቅላላ ዋጋ ብር 10,000 /አስር ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ቦሌ ክፍለ ከተማ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ዲዛይንና ግንባታ ፑል ፋይናንስ አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 215 በመምጣት ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር 300 /ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ለየብቻ አንድ ዋና እና አንድ ቅጅ በማድረግ በሰም በታሸጉ በተለያዩ ኢንቨሎፖች ፋይናንሻል እና ቴክኒካል ዋናውን ዋና/orginal/ እና ቅጅውን ቅጅ /copy/ በማለት በግልጽ በሚታይ ጽሑፍ በፖስታዎቹ ላይ በመጻፍ ማህተምና ፊርማ በማድረግ ከላይ በተጠቀሰው ቀን በቦሌ ክ/ከተማ ስፖርት ጽ/ቤት በመቅረብ በጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የሥራ ቀን የሚገባ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
7. ጨረታውን በ11ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ድረስ ብቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ጨረታው ታሽጎ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በክ/ከተማው 7ኛ ፎቅ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ይከፈታል፡፡ ሆኖም ግን 11ኛው ቀን የስራ ቀን ከሆነ ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያው የስራ ቀን የሚገባ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸውን ዕቃዎች ከአጠቃላይ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝና ከስፖርት ም/ቤቱ የግዥ ውል ስምምነት መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡
9. ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት ሳያሟሉ በጨረታ ላይ ለመሳተፍ መሞከር ከጨረታው ያሰርዛል፡፡
10. የጨረታው ውጤት ይፋ ከሆነ በኋላ ም/ቤቱ ጠቅላላ ለጨረታው ከቀረበው የእቃ ብዛት 20% ከፍና ዝቅ ብሎ የግዥ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
11. ለጨረታው የተሰጠው ዋጋ ለ60 ቀናት ጸንቶ ይቆያል፡፡
12. ም/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ተጫራቾች ይፋ በሚደረገው ውጤት ቅሬታ ካላቸው በ5 ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
14. ተጫራቾች ያሸነፉትን እቃ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፡፡
15. ተጫራቾች ያሸነፉትን እቃ ባቀረቡት ሳምፕል (ናሙና) መሰረት አይነትና ብዛት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በአድራሻችን በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 09 13 61 60 49/ 09 10 09 70 71 ደውለው ያነጋግሩን፡፡

ማሳሰቢያ፡- ሲፒኦ ሲዘጋጅ ቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት Bole sub city administration sport council በሚል ይዘጋጅ

አድራሻ፡- መገናኛ አደባባይ አጠገብ ቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 707 ስፖርት ጽ/ቤት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ክ/ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት

ልጆች፤ የምትማሩበትን ቁሳቁስ ምን ያህል በጥንቃቄ ትይዛላችሁ?

በፋንታነሽ ተፈራ

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? የትምህርት መሳሪያዎቻችሁን በአግባቡ መያዝ እንዳለባችሁ ምን ያህሎቻችሁ ተረድታችሁ ተግባራዊ ታደርጋላችሁ? በጉዳዩ ላይ ከጎደኞቻችሁ አልያም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ሀሳብ ተለዋወጡ እያልን የአፄ ናኦድ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ተሞክሮን አቅርበንላችኋል፡፡

ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ
ተማሪ ፍሬምናጦስ ምህረት

ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ
ተማሪ ብሌን ምትኩ

ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ
ተማሪ ፌቨን ታፈሰ

ፎቶ፦በገነት ወንድሙ
ተማሪ በረከት ይበቃል

ብሌን ምትኩ እባላለሁ። የ5ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 11 ዓመቴ ነው። ትምህርት የምማርባቸው ቁሳቁስ መጽሐፍ፣ ደብተር፣ እስክሪቢቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ እንዲሁም እነዚህን ነገሮች የምይዝበት ቦርሳ ናቸው። እነዚህን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ደግሞ በአግባቡና በስርዓት ነው የምይዛቸው፡፡ ይህም ማለት መጽሐፍትና ደብተሬን ከመቀደድና ከመበላሸት ለመጠበቅ አሽጌ እጠቀማለሁ፡፡ እስክሪቢቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫና የመሳሰሉትን ደግሞ እንዳይጠፉ በአግባቡ አስቀምጣለሁ፡፡

መማሪያ ቁሳቁሴን በአግባቡ ካልያዝኩ ሊጠፉ፣ ሊቀደድ እንዲሁም ሊበላሽ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ከእኛ ቀጥለው የሚማሩት ተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት እንዲያጡ በማድረግ ትምህርቱን በአግባቡ እንዳይማሩ ያደርጋቸዋል፡፡ የተበላሸውን ወይም የጠፋውን ቁስ ለመተካት አላስፈላጊ ወጭ ያስወጣል፤ በትምህርት ቤትም ውጤት ወይም ማርክ ያስቀንሳል፡፡

በረከት ይበቃል እባላለሁ፡፡ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 13 ዓመቴ ነው፡፡ የምማርባቸውን መጻሕፍትና ደብተር ሸፍኜ በንፅህና እይዛለሁ፡፡ ገፆችን አልቀድም፣ አላጥፍም፣ በላያቸው ላይም ጽሑፍም ሆነ ስዕል አልስልም። እስክሪቢቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ የመሳሰሉትን ደግሞ እንዳይሰበሩ፣ እንዳይጠፉና እንዳይበላሹ በማድረግ እጠቀማለሁ፡፡

አንድ ጊዜ ደብተሬን ለጓደኛዬ አውሼ በወቅቱ ባለመቀበሌ ጠፍቶብኛል፡፡ በዚህም ከቤተሰቦቼ ቁጣ እንዲሁም በድጋሚ እንድጽፍ ተገድጃለሁ፡፡ በመጻሕፍት ላይ መልሶችንና የተለያዩ ጽሑፎችን ስንጽፍ የቀጣይ ተማሪዎች የቤት ስራም ይሁን የክፍል ስራ በራሳቸው እንዳይሰሩ ስለሚያደርጋቸው ይህን አላደርግም፡፡

ፌቨን ታፈሰ እባላለሁ፡፡ 10 ዓመቴ ሲሆን የ4ኛ ክፍል ተማሪም ነኝ። የ3ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ የሂሳብ ደብተሬን በአግባቡ ባለመያዜ ጠፋብኝ፡፡ የሚሰጠውንም ትምህርት በአግባቡ ለመከታተል ተቸገርኩ። ቤተሰቦቼም አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጡ አደረግኳቸው፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከስህተቴ በመማር የተገዛልኝን አጋዥ መጻሕፍትም ሆነ መንግስት የሚሰጠኝን የመማሪያ ቁሳቁስ በአግባቡ እይዛለሁ፡፡ ቦርሳዬን ከቆሻሻና ከውሃ እጠብቃለሁ፡፡ ስሜን በመጻፍ ወይም የራሴን መለያ በማድረግ ከሌሎች ቁሳቁስ ጋር እንዳይቀላቀሉ አደርጋለሁ፡፡ ተምሬ ከጨረስኩ የቤት ስራ ከሰራሁም ሆነ ካነበብኩ በኋላ በቦታው አስቀምጣለሁ፡፡

ፍሬምናጦስ ምህረት እባላለሁ። የ6ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 12 ዓመቴ ነው፡፡ እንደተማሪነቴም የመማሪያ ቁሳቁሴን የማሟላትና በጥንቃቄ የመያዝ ኃላፊነት አለብኝ፡፡ ደብተር፣ መጻሕፍት፣ እስክሪቢቶ፣ እርሳስ፣ ማስመሪያና የመሳሰሉት መማሪያዎቼን በቦርሳዬ አስቀምጣለሁ፡፡ ጠዋትና ማታም ወደ ቦርሳ ማስገባቴን አረጋግጣለሁ። ለሌሎች በውሰት ከሰጠሁም ቶሎ እቀበላቸዋለሁ፡፡

አዲስ አበባ እና የሕጻናት መጫወቻ ቦታዎች

በአዲስ አበባ ከተማ በተከናወኑት የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች አማካኝነት ከተማዋን ንጹህና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች እና የአረንጓዴ ስፍራዎች የተሰሩ ሲሆን፤ ለህፃናት እና ለልጆች ትኩረት ተሰጥቶ ዘመናዊ የህፃናት መጫወቻ ቦታዎችም ተገንብተዋል።

የህፃናት መጫወቻ ቦታዎች መሰራታቸው ሕጻናት ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ መጪው ትውልድ በአካል እና በአእምሮ የዳበረ እንዲሆንም የህፃናት መጫወቻ ቦታዎች አስተዋጿቸው የጎላ ነው፡፡

ህጻናት እና ታዳጊዎች በዕረፍት ጊዜያቸው የሚዝናኑባቸው እነዚህ መጫወቻዎች በከተማዋ በተለያዩ ቁልፍ የኮሪደር መስመሮች ላይ ተደራሽ ሆነዋል።

በዚህም በከተማዋ 11 ብቻ የነበሩ የቀድሞ የሕጻናት መጫወቻ ቦታዎች በአሁኑ ወቅት ወደ 6ሺህ 70 አድጓል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ በቀጣይም የሕጻናት መጫወቻ ሥፍራዎችን ቁጥር ወደ 12 ሺህ የማድረስ ግብ አስቀምጧል፡፡

የመረጃ ምንጭ፡- የከአዲስ አበባ ኮሚኒኬሽን ቢሮ

10 ልዩነቶችን ፈልጉ



እንቆቅልሽ

ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

በትልቅ ምጣድ ትንሽ እንጎቻ

መልስ፡- ለ. ጨረቃ

የዚህ ሳምንት ጥያቄ

ቀይ ሙሽራ፤ በነጭ አጥር ታጥራ?

ሀ. ቪላ
ለ. ሆስፒታል
ሐ. ምላስ

ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

ቴክኖሎጂ ያቀናው የገቢ መንገድ

- ተቋሙ ከወረቀት አሰራር ወደ ዲጂታል እንዲሸጋገር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሚና የላቀ ነው

በደረጀ ታደሰ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማዘመንና ለማሻሻል ከዚህ ቀደም የጀመራቸውን ጥረቶች በከፍተኛ ፍጥነት አጠናክሮ ቀጥሏል። በተለይም የአገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማስደገፍ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ፍትሐዊ አገልግሎትን ለግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ለማድረስ የተሠራው ሥራ ውጤታማ መሆኑን ግብር ከፋዮች፣ የተቋሙ ሠራተኞች እና አመራሮች መስከረዋል።

ለከተማችን ብሎም ለሀገራችን ዕድገትና ብልጽግና የግብር ከፋዩ ማህበረሰብ አስተዋጽኦ ምን ያክል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ ማህበረሰብ ዕውቀቱን፣ ሃብቱን፣ ክህሎቱንና ጉልበቱን በማስተባበር በሚፈጥረው እና በሚሰማራበት ሥራ መስክ ለሀገር ዕድገት የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ ባሻገር ከሚያገኘው ገቢ ላይ የሚጠበቅበትን ግብር በመክፈል የዜግነት ግዴታውን ይወጣል። እንዲህ ያለው ዜጋ ሊከበር ይገባል፡፡ ከሠራው ሥራ ካገኘው ገቢ ግብር ለመክፈል ወደ ግብር ሰብሳቢ ተቋም ሲመጣ የሚሰጠው አገልግሎት ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ፍትሐዊ ማድረግ አንዱ የአክብሮት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ገቢዎች ቢሮ ተቋማዊ አቅሙን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ግብዓት ለማጠናከር ከተለያዩ አጋር ተቋማት ጋር በመተባበር የሠራውና እየሠራ ያለው ይህንን ታሳቢ በማድረግ ስለመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ለዝግጅት ክፍላችን አስረድተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ የገቢዎች ቢሮን በቴክኖሎጂ እንዲዘምን ካገዙ ተቋማት መካከል አንዱ ነው፡፡ በቢሮው ለምተው ለገቢዎች ቢሮ ለአገልግሎት ከበቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል፦ የዲጂታል ፋይል አስተዳደር ሥርዓት (DMS)፣ የስማርት ኦፊስ የሰነድ እና ደብዳቤዎች ማስተዳደሪያ ሥርዓት፣ የሰርቪሊያንስ ካሜራ (Surveillance Camera) እና አይፒ ስፒከር (IP Speaker) ይገኙበታል።

የዲጂታል ፋይል አስተዳደር ሥርዓት (DMS)

በገቢዎች ቢሮ የነበረው የቀድሞ የፋይል አስተዳደር ሥርዓት ሙሉ በሙሉ በወረቀት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ጊዜና ጉልበትን የሚያባክን፣ ለብልሹ አሠራር እና ለተገልጋይ ምሬት የሚዳርግ ኋላቀር አሰራር እንደነበር ያስታወሱት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የሶፍትዌር ኢንጂነር ጌታቸው በሪሁን፣ ይህ ለዲጂታል ፋይል አስተዳደር ሥርዓት (DMS) ቴክኖሎጂ መልማት መነሻ ሆኗል፡፡ ቴክኖሎጂው የለማበት እና ለአገልግሎት የበቃበት ዋና ዓላማ የግብር ከፋዮችን ሰነዶች በዲጂታል መልክ በአንድ ማዕከላዊ ቦታ በማደራጀት በወረቀት ላይ የተመሠረተ ኋላቀር የማህደር አያያዝን በዘመናዊ ኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ለመተካት የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እየሰጠ ነው

ሲስተሙ የታለመለትን ዓላማ ማሳካቱን የገቢዎች ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ መስክረዋል፡፡ እሳቸው እንዳብራሩት፣ የዲጂታል ፋይል አስተዳደር ሥርዓት (DMS)፤ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የተለየ ዲጂታል ማህደር በመክፈት ስካን የተደረጉ ሰነዶችን መጫንና መከታተል፣ በፍጥነት መፈለግና ማግኘት፣ መረጃዎችን በ Excel፣ CSV እና Print መልክ ማውጣት፣ እንዲሁም 18 ድርጅቶችን በአንድ ላይ ማስተዳደር አስችሏል። በተጨማሪም በሚና ላይ የተመሠረተ የተጠቃሚዎች አስተዳደር፣ የተሰረዙ ፋይሎች ክትትል እና ቀጥታ የሲስተም ክትትል በዳሽቦርድ የማድረግ አቅም አለው።

የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አክለው እንደገለጹት፤ የዲጂታል ፋይል አስተዳደር ሥርዓት (DMS) ከ4 ሚሊዮን በላይ ፋይሎችን በዲጂታል መልክ በማደራጀት የሰነድ ፍለጋ ጊዜን ከሰዓታት ወደ ሰከንዶች የቀነሰ፣ የሰነድ መጥፋትና የመበላሸት ስጋትን ያስወገደ እንዲሁም የወረቀትና የሎጂስቲክስ ወጪን በእጅጉ የቀነሰ ትልቅ ተቋማዊ ለውጥ አምጥቷል። ለግብር ከፋዮች ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት ከመስጠቱ ባለፈ የሠራተኞችን የሥራ ጫና ቀንሷል፤ ኦዲተሮች በየትኛውም ቦታ ሆነው የሚፈልጉትን ፋይል በሰከንዶች ውስጥ አግኝተው ኦዲቱን በጥራት እንዲያከናውኑ አስችሏቸዋል፡፡

የስማርት ኦፊስ የሰነድ እና ደብዳቤዎች ማስተዳደሪያ ሥርዓት

ለገቢዎች ቢሮ አገልግሎት እንዲሰጥ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የለማው የስማርት ኦፊስ የሰነድ እና ደብዳቤዎች ማስተዳደሪያ ሥርዓት ደግሞ፤ የተቋሙን የገቢና ወጪ ደብዳቤዎች ዝውውር ሙሉ በሙሉ ከወረቀት ነፃ በሆነ መንገድ በኮምፒዩተር መረብ ለማከናወን፣ የክትትልና ቁጥጥር አቅምን ለማሳደግ፣ የሥራ ፍጥነትን በመጨመር ለጉዳዮች የሚሰጠውን ምላሽ ለማፋጠን እንዲሁም የሰነድ ደህንነትን ከጥፋትና ከመበላሸት ለመጠበቅ ታስቦ የተዘጋጀ ዘመናዊ አሰራር ነው፡፡

ይህ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ገቢ ወይም ወጪ የሆኑ ደብዳቤዎችን እንደባህሪያቸው በመለየት፣ የአስቸኳይነት ደረጃን ሞልቶ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በማስተላለፍ፣ የሁኔታ ክትትል በማድረግ እና ጉዳዩ ሲጠናቀቅ ምላሽ የተሰጠው በማለት የመመዝገብ ግልጽ የአሰራር ሂደት ያለው ነው። በዚህ አሰራር አማካኝነት ደብዳቤዎችን በአካል ለማመላለስ ይፈጅ የነበረው ጊዜ መቆጠብ፣ የሰነዶች የመጥፋት ዕድል እንዲወገድ እና ለህትመት፣ ፎቶ ኮፒና ወረቀት የሚወጣ ተቋማዊ ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል። ተቋሙን ወደ ዘመናዊ፣ ፈጣን እና ወረቀት-አልባ አሠራር አሸጋግሯል፡፡ ተጠያቂነት እንዲሰፍንና የተገልጋዮች እርካታ እንዲሻሻልም አግዟል፡፡

የሰርቪሊያንስ ካሜራ እና አይፒ ስፒከር

የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ እንዳብራሩት፣ የሰርቪሊያንስ ካሜራ ለገቢዎች ቢሮና በሥሩ ለሚገኙ ቅርንጫፍ ተቋማት ደህንነት እንዲሁም ለሥራ እንቅስቃሴ ክትትል አገልግሎት የሚሰጥ የዲጂታል ምስል መቅረጫ ቴክኖሎጂ ነው። ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመሆን ለምቶ ለአገልግሎት የበቃው ይህ ቴክኖሎጂ፤ በ17ቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ውስጥ በሚገኙ እንደ ኦዲት፣ ደንበኞች አገልግሎት፣ አወሳሰን እና የገቢ ሂሳብ ሥራ ክፍሎች ላይ ተገጥሞል። በዚህም የሠራተኞችን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የሥራ አፈጻጸም መቆጣጠር እንዲሁም በግብር ከፋዮች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አላስፈላጊ መዘግየቶችና እንግልቶችን በመለየት መከላከል አስችሏል።

በቀጥታ ክትትል (Real-time Monitoring)፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው ምስል መቅረጽና ማስቀመጥ (HD/4K)፣ የእንቅስቃሴ መለያና ማንቂያ (Motion Detection & Alerts) እንዲሁም የሌሊት እይታ (Night Vision) የመሳሰሉ ጠንካራ ባህሪያት ያሉት ሲስተሙ የተቋሙን፣ የሠራተኛውን እና የደንበኞችን ደህንነት ከማስጠበቁም በላይ የሥራ ቦታ ሥነ-ሥርዓትን በማክበር ሠራተኞች በሥራ ሰዓት ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል። በአጠቃላይ ይህ የቴክኖሎጂ ውጤት የሥራ ፍሰት ግልጽነትን በመፍጠር፣ ፍትሐዊነትን በማስፈን፣ የደንበኛ አገልግሎትን በማሻሻል እና የውስጥ ቁጥጥር ሥራዎችን በማጠናከር የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን በመረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

የአይፒ ስፒከር (IP Speaker) የኔትዎርክ መሠረተ-ልማትን በመጠቀም ድምጽን በዲጂታል መንገድ የሚያስተላልፍ ዘመናዊ የድምጽ ማጉያ ቴክኖሎጂ ነው። ይህ ሲስተም በኢንተርኔት ገመድ ወይም በዋይ ፋይ (Wi-Fi) ከተቋም (ቢሮ) የኮምፒውተር ኔትዎርክ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ከአንድ ማዕከላዊ ሥፍራ በኮምፒዩተር ወይም በስልክ የተቀረጹ መልዕክቶችን ወደተለያዩ ክፍሎች ወይም ህንፃዎች ለማስተላለፍ ያስችላል። በተጨማሪም የተቀረጹ ማስታወቂያዎችን፣ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን እና አስቸኳይ መረጃዎችን አውቶማቲክ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ ይውላል።

በገቢዎች ቢሮ ለአገልግሎት የበቃው የአይፒ ስፒከር (IP Speaker) የሚሰጠው ጥቅም ሰፊ እንደሆነ አቶ ሰውነት ገልጸዋል። ቴክኖሎጂው ቢሮው በማዕከል፣ በቅርንጫፎች እና በወረዳዎች ያለውን ተቋማዊ የውስጥ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ እንዲያዘምን አስችሎታል። ከበላይ አመራር የሚተላለፉ የሥራ መመሪያዎችን እና መልዕክቶችን ሠራተኞች ከሥራ ገበታቸው ሳይንቀሳቀሱ ልክ በሬዲዮ እንደሚሰራጭ ዓይነት በተመሳሳይ ጊዜ ለማድረስ ጠቅሟል፡፡ በወር አንድ ጊዜ ከፍተኛ አመራሮች የሥራ መመሪያ የሚሰጡበትን ቋሚ ባህል ለመገንባት አግዟል። እንዲሁም የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን፣ የአሠራር መመሪያዎችን እና አዳዲስ መረጃዎችን ለሠራተኞችና ለተገልጋዮች በአንዴ ለማዳረስ በመጠቀሙ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ሲሆን፣ ከደህንነት ሥርዓቶች (እንደ ሰርቪሊያንስ ካሜራዎች) ጋር በመቀናጀትም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በድምጽ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ለመስጠት ያስችላል።

በሽሮሜዳ የባሕል ልብስ በመሸጥ የንግድ ሥራ የተሠማሩት አቶ መስፍን በዳዳ በገቢዎች ቢሮ የተደረገውን የዲጂታል ለውጥ አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት፦ “ከዚህ ቀደም ግብር ለመክፈል፣ ክሊራንስ ለማግኘት ወይም ሰነድ ለማስተካከል ስንመጣ ለቀናት በመዝገብ ቤት በር እንመላለስ ነበር። አሁን ግን በዲጂታል ፋይል አስተዳደር (DMS) እና በኦንላይን አገልግሎቶች አማካኝነት የቲን ቁጥራችንን በመጠቀም በደቂቃዎች ውስጥ አገልግሎት ማግኘት ችለናል። ሰነዶቻችን ደህንነታቸው ተጠብቆ በመቀመጣቸው እና የቢሮው አሰራር በካሜራና በዘመናዊ ሲስተም በመደገፉ የሰራተኞች አቀባበልና ፍጥነት እጅግ ተሻሽሏል” በማለት ለውጡን አድንቀዋል፡፡

በከተማዋ እየተተገበረ ላለው የስማርት ሲቲ ርዕይ ስማርት ኢኮኖሚ እጅግ ወሳኝ ምሰሶ ነው። የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ እና የገቢዎች ቢሮ ትብብር የከተማዋን የኢኮኖሚ አቅጣጫ ወደ ዲጂታል ውህደት እያሸጋገረው ይገኛል፡፡ በዚህም የገቢዎች ቢሮ በማዕከል፣ በ17 ቅርንጫፎች እና በ114 ወረዳዎች ያሉትን ከ8 ሺህ በላይ ሠራተኞችና አመራሮች የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረጉም ባሻገር የግብር አሰባሰብ ሂደቱ በዲጂታል መሣሪያዎችና በመረጃ (Data-driven) እንዲመራ አቅም ፈጥሯል፡፡ ይህ ጅምርም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተደጋጋሚ መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

መለያ ቁጥር 01/2019

በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2019 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የደንብ ልብስ፣ ጨርቅ፣ ስፌት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ፈርኒቸር እቃዎች፣ስቴሽነሪ/የፅህፈት መሳሪያ፣ አላቂ የትምህርት እቃዎች፣ አላቂ የቢሮ እቃዎች፣ ሌላም አላቂ እቃዎች፣ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች እና ህትመት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

ስለሆነም በጨረታው ለመወዳደር የምትፈልጉ ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡትን መስፈርት የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በጨረታው እንድትሳተፉ እንጋብዛለን።

1. አገልግሎቱን እና እቃውን በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ብቃት ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው እና 2019 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው።
2. ተወዳዳሪዎች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
3. ተወዳዳሪዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆኑ ለዚህም የተመዘገቡበትን ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
4. ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋጋ፡-

   ሎት 1- የደንብ ልብስ እና ልብስ ስፌት 30,000.00
   ሎት 2- አላቂ (ዕቃዎች) የቢሮ እቃዎች 20,000.00
   ሎት 3- አላቂ የትምህርት እቃዎች 5,000.00
   ሎት 4- አላቂ እቃዎች እና አቅርቦቶች፡- ልዩ ልዩ መሳሪያዎች 15,000.00
   ሎት 5- የቢሮ ፈርኒቸር እቃዎች 50,000.00
   ሎት 6- ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች 100,000.00
   ሎት 7- ህትመት 5,000.00

5. ተወዳዳሪዎች የጨረታውን ዝርዝር ሰነድ ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት በሚገኘው ህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት መውሰድ ይችላሉ።
6. ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ናሙና ለሚቀርብላቸው እቃዎች ናሙና ያቀረቡ ብቻ የሚወዳደሩ ሲሆን ለቋሚ እቃዎች ስፔስፊኬሽን ማቅረብ ግዴታ ነው።
7. ተወዳዳሪዎች በዝርዝር የጨረታ ሰነድ ላይ በተዘጋጀው የዋጋ ዝርዝር መሙያ ላይ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው። በሌላ ሰነድ የሞላ ተቀባይነት የለውም።
8. ባቀረቡት የዋጋ ዝርዝር ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ማካተት አለባቸው።
9. ትምህርት ቤቱ በሚገዛው እቃ ላይ 20% የመጨመርና የመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው።
10. ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለአስር (10) ተከታታይ የሥራ ቀናት ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዳቸውን የመጀመሪያውን ፎቶ ኮፒ በፖስታ በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
11. በአስረኛው ቀን እስከ 11:30 ሰዓት ብቻ ይገባል፡፡
12. በአስራ አንድኛው ቀን በ4:30 ሰዓት ተወዳዳሪዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ ሳጥኑ ይከፈታል። ጨረታው የሚከፈትበት 11ኛው ቀን የበዓል ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆነ በቅርቡ ባለው የሥራ ቀን ይከፈታል።
13. የጨረታ አሸናፊው የሚያሸንፈው ነጠላ ዋጋ ነው።
14. አሸናፊዎች ያሸነፉበትን እቃ በራሳቸው ትራንስፖርት እስከ ትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው።
15. የጨረታ አሸናፊው ማሸነፉ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት /5/ የሥራ ቀናት ውስጥ የውል ማስከበሪያ ባሸነፈው እቃ ላይ 10% CPO ማስያዝ የሚችል መሆን አለበት።

ማሳሰቢያ፡-

- ትምህርት ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
- ሁሉም እቃ አዲስ መሆን አለበት።
- ናሙና እስከ 10 ቀን ብቻ የምንቀበል ይሆናል።
- ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ካስፈለጋችሁ በስልክ ቁጥር 0118 69 87 84 ደውለው ማግኘት ይችላሉ።

አድራሻ፡- በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ጎማ ቁጠባ ፊት ለፊት ወይም ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፊት ለፊት በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የህዳሴ ልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ልደታ ክ/ከተማ ት/ፅ/ቤት
ህዳሴ ልደታ 2ኛ ደ/ት/ቤት

የመዝናኛ ክበባትን ኦዲት ለማስደረግ የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

አውቶብስ ተራ ሁለገብ ሸማቾች ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ሶስት ያህል መዝናኛ ተቋማትን የ2018ዓ.ም የአንድ ዓመት የሒሳብ ስራዎችን የሚያሳይ ኦዲት ግልፅ ጨረታ በማውጣት ኦዲት ማስደረግ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በኦዲተርነት የሙያ መስክ መስፈርቱን የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች እንድትወዳደሩ በግልፅ ጨረታ የጋበዝን መሆናችንን እየገለፅን ለመወዳደር መሟላት ያለባቸው መስፈርቶችም፡-

1. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ሥራ ፍቃድ ያለው
2. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/Tin Number/ ያለው
4. ለመንግስት የሚጠበቅበትን ግብር የከፈለ
5. ከዚህ በፊት በኦዲት ሙያ ተሰማርቶ የነበረ እና የስራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል በተለይም ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር ተያያዥ ስራዎች ስለመስራቱ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል
6. የኢትዮጵያ ሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ፈቃድ የሰጣቸው ዝርዝር ውስጥ በኦንላይን የተመዘገበ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል
7. ሁለትና ከዚያ በላይ ኦዲት አድራጊ ባለሙያ ህብረት ሥራ ማህበሩ በሚገኝበት ቦታ መድቦ ማሰራት የሚችል እና በውል በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ምርመራውን አጠናቆ ሪፖርቱን በጥራት ማቅረብ የሚችል፡፡
8. የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/09፣ የህ/ሥ/ማ ደንብ ቁጥር 171/2016፣ የህብረት ሥራ ማህበራት የውክልና ኦዲት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 978/2016 እና ሌሎች ማስፈጸሚያ መመሪያና ደንቦችን ለመተግበር ፈቃደኛ የሆነ
9. የሚጫረቱበትን 2% የጨረታ ማስከበሪያ C.P.O ወይም በባንክ የተረጋገጠ ጋራንቲ ማስያዝ የሚችሉ
10. ጨረታውን ካሸነፉ የውል ማስከበሪያ 10% C.P.O ወይም በባንክ የተረጋገጠ ጋራንቲ ማስያዝ የሚችሉ
11. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኃላ የሰጠውን ዋጋ መለወጥ/ማሻሻል አይችልም።
12. ያሸነፉ ተጫራቾች ጨረታው ከተከፈተ በኃላ ከውድድሩ ሊወጡ አይችሉም።
13. የመንግስትን የፋይናንስ መመሪያ የሚጥስ ማንኛውም ነገር ተቀባይነት የለውም።
14. የኦዲቱ ስራ እንደተጠናቀቀ ሪፖርቱን ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት አቅርቦ ካስተቸ/ካስገመገመ/ በኋላ ለስራ አመራር ቦርዱ የሚያቀርብ እንዲሁም ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ለማንበብና ለማስረዳት ፈቃደኛ የሆነ
15. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 500 ብር በመክፈል መግዛት የሚችል እና የማህበሩ ስራ አመራር ኮሚቴ በሚያቀርበው የውል ሰነድ ህጋዊ የውል ስምምነት መዋዋል የሚችል ሆኖ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ 10 ተከታታይ የስራ ቀናቶች ውስጥ የጨረታ ሰነዱን አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 6 አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ት/ቤት ጀርባ በሚገኘው የህ/ሥራ/ማህበሩ ጽ/ቤት በመግዛት መጫረት የሚችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- ህብረት ሥራ ማህበሩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

- ጨረታው በቀን 18/02/19 ዓ/ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት በህብረት ሥራ ማህበሩ ጽ/ቤት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል ነገር ግን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ካልተገኙ ማህበሩ ለመክፈት አይከለከልም።

አውቶቢስ ተራ ሁለገብ ሸማቾች ኃላ/የተ/ህ/ስራ ማህበር

አድራሻ፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አዲስ ከተማ ት/ቤት ጀርባ በሚገኘው የህ/ሥራ/ማህበሩ ጽ/ቤት። ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 0973-73 73 36/ 0911-11 11 65 ይደውሉ፡፡

በአ/ከ/ክ/ከ ወ/07 አውቶብስ ተራ ሁለገብ ሸ/ኃ/የተ/የህ/ሥ/ማ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚቀርብ

የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ተምሳሌትነት

በለይላ መሀመድ

ፎቶ-ከገፀ ድር

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እገዛ ያደረጉ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች

ከአንድ ወር በፊት የካርታ መረጃዎችን እና የሰው ሰራሽ አስተውሎትን በመጠቀም የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣቸውን ስጋቶች በመተንበይና በመተንተን የሚታወቀው አልፋጅኦ (AlphaGeo) የተባለ ዓለም አቀፍ ኩባንያ እ.ኤ.አ. የ2026 የከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ ስጋትና የመቋቋም አመላካች (Climate Risk & Resilience Index) ጥናት ይፋ አድርጎ ነበር፡፡ ጥናቱ ከተካሄደባቸው 72 ትላልቅ ከተሞች አዲስ አበባ የአየር ንብረት ለውጥ ስጋቶችን በመቋቋም አቅም ከዓለም ሁለተኛ፤ ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች፡፡

ጥናቱ ከተሞች ለተፈጥሯዊ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎች ያላቸውን ተጋላጭነት እና ስጋቶችን ለመቀነስ የተወሰዱ የመቋቋሚያ እርምጃዎች ውጤታማነትን፣ ለጎርፍ፣ ለከፍተኛ ሙቀት፣ ለድርቅ፣ ለሰደድ እሳት እና ለአውሎ ነፋስ ያላቸውን ተጋላጭነት ፈትሿል፡፡ እንዲሁም እነዚህን አደጋዎች ለመቋቋም በማኅበረሰብ እና በመሠረተ ልማት ደረጃ ያላቸው ዝግጁነት ታይቷል።

ዛሬ የከተሞች ጥንካሬ የሚለካው በሕንፃ ቁመት ወይም በመንገድ ርዝመት ብቻ አይደለም። ጎርፍ ቢመጣ ምን ያህል ይጎዳሉ? ሙቀት ቢጨምር ነዋሪዎቻቸውን እንዴት ይጠብቃሉ? የውሃ እጥረት ቢከሰት ምን ያህል ዝግጁ ናቸው? አየር ቢበከል ምን ያህል ፈጣን ምላሽ ይሰጣሉ?... የሚሉት ጥያቄዎች እየገዘፉ መጥተዋል። አዲስ አበባም ከዚህ የሚያስደንቅ ደረጃ ላይ ልትደርስ የቻለችው አደጋ ለመቀነስ ያላት የመላመድና የመቋቋም አቅም ጭምር ተመዝኖ እንደሆነ በጥናቱ ተመላክቷል።

አዲስ አበባ ይህንን ደረጃ ልታገኝ የቻለችው በተፈጥሮ ካላት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ባለፈ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ የተገበራቸው የተለያዩ የአየር ንብረት ማላመድ ስራዎች፣ በተለይም በቅርቡ የተወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎች እና የተቀናጁ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ግንባታዎች ናቸው:: የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የኮሪደር ልማት፣ የአረንጓዴ ልማት መስፋፋት እና የውሃ መፍሰሻ ሥርዓቶችና ሌሎች የከተማ መሠረተ ልማት ሥራዎች የአየር ንብረት ለውጥን መላመድ የሚያስችል አቅም ፈጥረዋል፡፡

የከተማዋ የተፈጥሮ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ ሲታይ በተራራማ ስፍራ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለአውሎ ነፋስ እና ለባህር ዳርቻ የሙቀት ማዕበል ያላት ተጋላጭነት በጣም አነስተኛ ነው።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አስተዋጽኦ ያደረጉ የአካባቢ ልማት ስራዎችን በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአየር ንብረት ለውጥና አማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር ተወካይ እንዲሁም የባዮ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማሻሻልና ማስፋፋት ቡድን መሪ አቶ እንዳለ ፍቃዱ ተከታዩን ሀሳብ ሰጥተውናል፡፡

> ከላይኛው ተፋሰስ ከእንጦጦ ጀምሮ እንደ ቀበና፣ ግንፍሌ የመሳሰሉ ወንዞች በቆሻሻ ምክንያት ተደቅኖባቸው ከነበረው የመበከል አደጋ ጸድተው ወደቀድሞ የተፈጥሮ ይዘታቸው እንዲመለሱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል

እንደ አቶ እንዳለ ማብራሪያ፣ የኮሪደር እና አረንጓዴ ልማት የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ይይዛል፡፡ በከተማዋ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተካሄዱ ሰፊ የኮሪደር ልማት ስራዎች ሰፋፊ የእግር መንገድ፣ የብስክሌት መስመሮች፣ የተለያዩ ፓርኮች እና የአካባቢ ጥበቃ በተለይም በመንገድ ዳር እና አካፋዮች የአረንጓዴ ልማት ስራዎች በስፋት ተሰርተዋል፡፡ ይህም የከተማዋን የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ እና የአየር ሁኔታን ለማመጣጠን ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ወንዞች እና የወንዝ ዳርቻዎች እንዲያገግሙም የወንዝ ዳር ልማት ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል፡፡ ከላይኛው ተፋሰስ ከእንጦጦ ጀምሮ እንደ ቀበና፣ ግንፍሌ የመሳሰሉ ወንዞች በቆሻሻ ምክንያት ተደቅኖባቸው ከነበረው የመበከል አደጋ ጸድተው ወደቀድሞ የተፈጥሮ ይዘታቸው እንዲመለሱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። እንደዚህ አይነት ተፈጥሮን የመጠበቅ ስራ በመሰራቱ የከተማዋን የጎርፍ አደጋ ተጋላጭነት ቀልብሰዋል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እና የዛፍ ተከላ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ፋይዳው የገዘፈ እንደሆነ አቶ እንዳለ አንስተዋል፡፡ ዛፎችና አረንጓዴ ቦታዎች ለከተማ ውበት ብቻ ሳይሆን ለጥላ፣ ለከተማ ሙቀት መቆጣጠር፣ ለውሃ መሳብና ለአካባቢ ጥራት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ለዓመታት የተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ በከተማዋ የደን ሽፋን እንዲጨምር በማድረግ ዓለም አቀፍ ስጋት እየሆነ የመጣው የሙቀት ተጽዕኖ እንዲቀንስ አድርጓል ብለዋል።

መንግስት በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ደረጃ በደረጃ በማስቀረት ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ለመሸጋገር ፖሊሲ መቅረጹ በተመሳሳይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፡፡ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማበረታታት መንግስት የከተማዋን የአየር ብክለት በመቀነስ አየር ንብረቱ ምቹ እና ተስማሚ እንዲሆን እድል መፍጠሩን የገለጹት አቶ እንዳለ፣ የአየር ብክለትና የአየር ንብረት ቀውስ በብዙ መንገዶች ይገናኛሉ። በተለይ ከተሞች በትራንስፖርት፣ በሕንፃ፣ በኢንዱስትሪና በቆሻሻ አያያዝ የሚመነጩ ልቀቶችን በመቀነስ በአንድ ጊዜ የአየር ጥራትንና የአየር ንብረት ግቦችን ሊያሳኩ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

የዓለምን የአየር ንብረት ቀውስ ለመከላከል፣ የበካይ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ እና በአረንጓዴ ልማት ላይ በጋራ ለመስራት የተመሰረተው የዓለም ትላልቅ ከተሞች ኔትዎርክ (C40) የ2025 ሪፖርት አዲስ አበባ በአየር ጥራት መሻሻል እያሳየች መሆኑን ይጠቁማል። በፈረንጆቹ 2026 ደግሞ አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከተሞች ውስጥ የሚከሰተውን የአየር ብክለት ለመቀነስ እና የህዝብ ጤናን ለማሻሻል የተመሰረተ ብሪዝ ሲቲስ (Breathe Cities) የተሰኘ ዓለም አቀፍ ተነሳሽነት ውስጥ እንደተካተተች ይፋ ተደርጓል። የዚህ ሁሉ ጥረት ድምር ውጤት አዲስ አበባን ዓለም ላይ ከሚገኙ 72 ከተሞች የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም አቅም ከቺካጎ ቀጥላ በዓለም 2ኛ ደረጃ ላይ እንድትቀመጥ እንዳደረጋት አብራርተዋል፡፡

ያገኘችው ደረጃ ስላለው እንድምታ

እንደ አቶ እንዳለ ገለጻ፤ የመጀመሪያው አንድምታ የከተማዋ ልማት ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተነጣጥሎ ሊታይ እንደማይገባ ማሳየቱ ነው። መንገድ ግንባታው፣ የወንዝ ዳር ልማቱ፣ የአረንጓዴ ቦታ መስፋፋቱ፣ የውሃ ማፋሰሻው... የከተማዋን የአየር ንብረት የመላመድ አቅምን የሚያጠናክሩ እና ለቀጣይ መነቃቃትን የሚፈጥሩ ናቸው። ይህን ደረጃ አስጠብቆ መሄድ ቀጣዩ የቤት ስራ ነው፡፡ ስለዚህ የአዲስ አበባ ቀጣይ ጉዞ የሚመራው በልማቱ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በነዋሪዎቹ ሕይወት ላይ በሚፈጥረው ተጨባጭ ለውጥ መሆን አለበት።

አዲስ አበባ ዛሬ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም አቅም ከአፍሪካ ቀዳሚ ናት፤ በዓለምም ከቺካጎ ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ተቀምጣለች። ይህ የሚያኮራ ነው። የዛሬው ደረጃ ነገ የተሻለች፣ የተረጋጋችና ለነዋሪዎቿ የተመቸች ከተማ ለመገንባት ፋይዳው የጎላ ነው።

ሁለተኛው አንድምታ ደረጃው የአዲስ አበባን ስም በዓለም አቀፍ የከተማ ውይይት ውስጥ ከፍ እንደሚያደርግ አቶ እንዳለ ያነሳሉ፡፡ የአልፋጂኦ ጥናት በተለይ የከተማ አደጋን ከመላመድ አቅም ጋር በማጣመር የሚመለከት በመሆኑ ውጤቱ ለከተማ ልማት ዕቅድ አውጪዎችና የአየር ንብረት ፋይናንስ ተዋናዮችን ለመሳብ የሚያግዝ እንደሆነ እና ይህም የደረጃው ሌላኛው አንድምታ መሆኑን አቶ እንዳለ አብራርተዋል ።

ከወንዝ ዳርቻ እስከ ኮሪደር፣ ከዛፍ እስከ ንጹሕ አየር፣ ከትራንስፖርት እስከ ጎርፍ መከላከያ... የከተማዋ የአየር ንብረት ጽናት በብዙ የሚጻፍ ታሪክ ነው። የዛሬው ደረጃ ለአዲስ አበባ የሚሰጠው ትልቁ መልዕክትም የተገኘውን ደረጃ ማክበር ብቻ ሳይሆን የበለጠ ጽኑ፣ አረንጓዴ፣ ንጹሕና ለነዋሪዎቿ የተሻለች ከተማ ለመገንባት መጠቀም ነው።

ለንግዱ ... ከገጽ 6 የዞረ

ተደርጓል፡፡

ለንግዱ ማህበረሰብ የተሻለ እና ዘመናዊ አገልግሎት ለማድረስ ቢሮው አሠራሩን በቴክኖሎጂ የማዘመን፣ የሠው ኃይል አቅሙን የማሳደግ፣ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን የመከላከል እንዲሁም በጥናትና ምርምር የተመሰረተ የውሳኔ አሠጣጥ የማዳበር ተግባራት ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ የቢሮው ኃላፊ አስረድተዋል፡፡ የንግድ አሰራር ሥርዓትንና አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ከማድረግ አንፃር፣ የኦንላይን ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን አጠናክሮ ማስቀጠል እና ሌሎች አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲሰጡ ከማድረግ ባሻገር፣ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት የኢኮሜርስ ባህልንና ቁጥጥር ስርዓትን ማሳደግ፣ ዲጂታል የንግድ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ህገ-ወጥነትን መከላከል፣ ሁሉንም የአገልግሎት ክፍያዎች በኢ-ክፍያ (Tele-Birr, CBE Birr እና ሌሎች ባንኮች) ብቻ እንዲፈጸሙ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

ውጤታማ የሰው ኃይል አስተዳደርን በመተግበር በአፈጻጸማቸው ብቁ የሆነ አገልግሎት ሠጪ አመራሮችን ፈፃሚዎችን አቅም መገንባት ሌላኛው ተቋሙ ትኩረት የሚያደርግበት ጉዳይ መሆኑን በመጠቆም፣ በክህሎትና በሥነ-ምግባር የታነፀ፣ ለተገልጋይ ቅድሚያ የሚሰጥ የሰው ኃይል መገንባት፣ ሠራተኞች አዳዲስ የንግድ ቴክኖሎጂዎችንና ዘመናዊ የአሰራር ስልቶችን እንዲላመዱ ቀጣይነት ያለው ስልጠና መስጠት፣ የሠራተኞችን አፈፃፀም በቁጥርና በውጤት (KPI) በመመዘን፣የተሻለ ለሰሩት እውቅና የሚሰጥበት ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አጠናክሮ ለማስቀጠል ታቅዶ ወደ ተግባር መገባቱን አብራርተዋል፡፡

“ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ‘ዜሮ ሙስና' ቢሮ መፍጠር እንደ ተቋም አቋም የተያዘበት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በመጠቆም፤ ይህንን ውጤታማ ለማድረግ የሚተገበሩ ዝርዝር ተግባራትን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡ እንደ ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ በአገልግሎት አሰጣጡ ከህብረተሰቡ የሚቀርቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቀነስ፣ ማንኛውም አገልግሎት የሚፈጅበትን ጊዜና መስፈርቶች ለህዝብ ግልጽ ማድረግ፣ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማገናኘት በተገልጋይና በሠራተኛ መካከል ያለውን ቀጥተኛ ንክኪ በማስቀረት የሌብነት አስተሳሰብና ድርጊቶችን ማጥፋት፣ ነጋዴዎችና ሸማቾች የሚያጋጥሟቸውን ብልሹ አሰራሮች በቀጥታና በምስጢር ለበላይ አካል የሚያሳውቁበት ዲጂታል መድረክ ማዘጋጀት በትኩረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የውሳኔ ሰጪው አካል ወይም ከፍተኛ አመራሩ በተጨባጭ መረጃ ውሳኔ እንዲሰጥ፣ አዲስ የሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ የንግድ ሕጎች ውጤታማነታቸው እንዲጎላ ተግባራት በጥናትና ምርምር እንዲሁም የዘርፉን ባለድርሻ አካላት በተገቢ መልኩ ያሳተፈ እንዲሆን ይደርጋል፡፡

የቅጠል ... ከገጽ 8 የዞረ

እንደሚገኙ ዳንኤል (ዶ/ር) ያብራራሉ፡፡

በልማቱ ቢሮዎች ብቻ ሳይሆኑ መኖሪያዎች፣ ንግድ ቦታዎች፣ መዝናኛና ሌሎች አገልግሎቶች በአንድ አካባቢ ሲገናኙ ከተማዋ የበለጠ ንቁ ትሆናለች። ሰው ባለበት ቦታ ሕይወት አለ። ሕይወት ባለበት ደግሞ ከተማ አለ ሲሉም አክለዋል፡፡

አዲስ አበባ የ24 ሰዓት ንቁ እንቅስቃሴ የምታደርግ ከተማ እየሆነች መምጣቷ፣ ቱሪዝሟ እና ዲፕሎማሲዋ እንዲያድግ ብሎም አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሚናዋን በአግባቡ እንድትወጣ እያደረጋት ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሰሞኑ የበጀት ዓመቱን የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ገምግሟል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ የከተማዋ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው በአጋሩት መረጃ፣ በ90 ቀናት ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል የቤቶች ግንባታንና የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን የማሻሻል ሥራ ይገኝበታል። በዚህም ዜጎች ንጹሕና ክብራቸውን የሚጠብቁ ቤቶች እንዲያገኙ መሰራቱንና በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡

ከትውልድ... ከገጽ 9 የዞረ

የጽዳት ሠራተኛ እና ሦስት የጥበቃ ባለሙያዎች አሉት። ማዕከሉ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ወጪ የተገነባ እና የሚተዳደር ሲሆን፤ አገልግሎቱን በይፋ የጀመረው መስከረም ወር 2018 ዓ.ም. ነው። በአሁኑ ወቅት በማዕከሉ 500 ህጻናት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ማዕከሉ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ህጻናት በአካልና በአዕምሮ እንዲጎለብቱ እንዲሁም በልጆቻቸው እንክብካቤ ምክንያት ቤት ውስጥ ተቀምጠው ሥራ ማግኘት ያልቻሉ እናቶችን ወደ ሥራ ማስገባት፣ ገቢ እንዲያገኙና ራሳቸውን እንዲችሉ ማስቻል እንደሆነ አብራርተዋል።

አቶ አዳነ አክለውም፤ ማዕከሉ አገልግሎት የሚሰጠው ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል እስከ 11 ሰዓት ተኩል እንዲሁም ቅዳሜ ከ2 ሰዓት ተኩል እስከ ስድስት ሰዓት ተኩል ድረስ ነው። ህጻናቱ በቆይታቸውም በፕሮግራም የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ተረት ይሰማሉ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይገጣጥማሉ፣ ይጫወታሉ፣ የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፣ ችግኞችን ያጠጣሉ፣ ይተኛሉ እንዲሁም ይመገባሉ።

አስተባባሪው አያይዘውም፤ የማእከሉ መቋቋም ህጻናቱ በንጽህናና በእንክብካቤ እንዲውሉ በማድረግ አካላዊና አእምሯዊ እድገታቸው እንዲሻሻል ከማስቻሉም በተጨማሪ ከሌሎች ጋር መጫወትን፣ ዕቃ መጋራትን፣ ሌሎችን ማዳመጥን፣ መከባበርን፣ መቻቻልንና በቡድን መስራትን እየተማሩ እንዲመጡ እድል ፈጥሮላቸዋል። እናቶች ደግሞ "ልጄን ማን ይይዝልኛል" ከሚል የዕለት ተእለት ጭንቀት ተላቅቀው ስራቸውን በነፃነት ማከናወን ጀምረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ማዕከሉ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት በዋናነት ህፃናትን መንከባከብ የዛሬን ችግር መፍታት ብቻ ሳይሆን፤ የነገን ትውልድ መገንባት መሆኑን በመገንዘብ ክፍለ ከተማው ጋር በመነጋገር ወላጆቻቸው ቋጥረው የሚያመጡትን ምግብ ከጠዋት እስከ 6 ሰዓት ምሳ ድረስ እንዲጠቀሙ ከተደረገ በኋላ 9 ሰዓት መክሰስ ሰዓት ላይ ደግሞ ሴሪፋም እንዲመገቡ ይደረጋል። ከጤና ጣቢያዎች ጋር ትስስር በመፍጠርም ከክብደት በታች ለሆኑ ህጻናት አልሚ ምግብ በመስጠት አካላዊ እድገታቸው የተስተካከለ እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት ከ100 በላይ ሕፃናት ወደ ማዕከሉ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ ናቸው። በተጠባባቂነት የሚገኙ ህጻናትን ተጠቃሚ ለማድረግ አራት ዓመት ሞልቷቸው ወደ ትምህርት ቤት በሚገቡ ልጆች የማተካካት ስራ እንደሚሰራ አስተባባሪው ተናግረዋል።

በህጻናት ላይ መስራት ትውልድን ማነጽ ማለት ነው። ህጻናት በጋራ ሲያድጉ በውስጣቸው አብሮነትን፣ መቻቻልን፣ መከባበርንና ቅድሚያ መሰጣጣትን እየተለማመዱ ይሄዳሉ። ይህ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2ን ጨምሮ በህጻናት ማቆያዎች የተጀመረው በጎ ጅምር በግል ሴክተሮችም ሆነ በሌሎች የመንግስት አካላት ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው የትውልድ ግንባታ መሰረት ነው። ይህ እድል አሁንም እርዳታ ለሚፈልጉ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተስፋ ሆኖ እንዲቀጥል ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ከከንቲባ ጽህፈት ቤት ማህበራዊ ሚዲያ ባገኘነው መረጃ መሰረት፤ ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ ከተማ አዲስ አበባ፤ ዓለም አቀፍ ሽልማት ተቸሯታል። የመሸለሟ ምስጢር በብዙ መልኩ የሚገለጽ ነው፡፡ ከተማዋ አገር ተረካቢው ትውልድ በሁለንተናዊ መመዘኛ ተመችቶት የሚያድግባት እንድትሆን አስደናቂ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በመሠራትም ላይ ናቸው፡፡ በመዲናዋ የመጫወቻ ስፍራዎች እና የሕፃናት ማቆያዎች በብዛትና በጥራት ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል። የሕዝብ የሕፃናት ማቆያዎች ከ11 ወደ 1 ሺህ 100 ደርሰዋል። በተለያዩ ሞዴሎች የተደራጀው የሕጻናት ማቆያ ቁጥር በጥቅሉ 1 ሺህ 155 የደረሰ ሲሆን፣ 27 ሺህ 302 ሕፃናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተግባራዊ የሆነው የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም በመዲናችን የሚገኙ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ገደማ ሕፃናትን እንዲሁም 330 ሺህ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ታዳጊዎች ተደራሽ ለማድረግ ዓላማ ማድረጉ ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል፡፡

አዲስ አበባ ዛሬ ዓለምን ያስገረመችው እና የትኩረት ማዕከል የሆነችው በውብ የኮሪደር ልማቷ፣ በወንዝ ዳርቻዎቿ ውበት፣ ወይም በሌሎች ፕሮጀክቶቿ ብቻ አይደለም። ብሩህ አእምሮ ያለው ጤናማ ትውልድ በማፍራት፣ ህፃናትን ለማሳደግ ምርጧ ከተማ መሆኗን በተግባር በማሳየትና የዜጎችን በተለይም የሕፃናትን ሕይወት በሚቀይር የሰብዓዊ ልማት ሥራዋ ጭምር ነው። ይህ በሰብዓዊነት እና በትውልድ ላይ የተደረገው ጥልቅ ኢንቨስትመንት የመንግስትን የመደመር እሳቤ ወደ ተግባር የቀየረ፣ ዜጎችን በአንድነት አስተባብሮ ከተማዋን እውነተኛ የብልፅግና ተምሳሌት ያደረጋት ነው፤ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን በተደጋጋሚ እንድትቀዳጅ ያስቻላት ዋነኛ ሚስጥርም ይኸው መሆኑን ከከንቲባ ጽህፈት ቤት የማህበራዊ ድህረ ገጽ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የመንግስት ምስረታ ወቅት ከንቲባ አዳነች አቤቤ የቀጣይ አመት አስተዳደር ልዩ ትኩረት የሚቸራቸውን ስራዎች ዘርዝረዋል። በንግግራቸውም ልጆች ቦርቀው የሚያድጉበት ከተማ ትሆን ዘንድ የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራምን የማጠናከር ስራ እንደሚሰራ ገልፀዋል። ይህም ከተማዋ የትውልድ ግንባታ ላይ አሁንም በትኩረት መስራቷን እንደምትቀጥል አመላካች ነው፡፡

በጥበብ... ከገጽ 11 የዞረ

“...ተግ ሲል ያንቺ ሽውታ
ብዥ ሲል እንደ አድባር ጥሪ፣ እንደተርብ ቅርስ ሽታ
እንደ እሳት ዳር ተረት፣ እንደ እንቆቅልሽ ትውስታ
የጥቅምት እሸት አሸቶ፣ ነቃ ደሞ ያንቺ ትዝታ...
አውድማው ተንተረከከ
ሰንበሌጥ ተንተረከከ
ነይ አክርማ እንነቃቀል
ከወንዛችን ሾላ ጠለል
ነይ ጢሎሽ እንንጠላጠል
መስኮቻችን ሰብሎቻችን፥ ግጦሾቻችን አባቱ
የእቴቴሽ ላሞች አጋቱ
በሮቻችንም አጓሩ፣ ኮርማዎቻችንም ነቁ
ጊደሮቻችን ለጥቃት፣ ለይዘታ ለክብደት በቁ
የሁዳድ ድርቆሽ ሰፈር፣ ጥገቶቻችን ቦረቁ...

እያለ ጥቅምትን ስዕላዊ በሆነ፣ ወቅቱን በሚያስናፍቅና በትዝታ በሚያስረቀርቅ መንገድ ከትቦታል፡፡ ከዚህ አንጻር ወርሃ ጥቅምት የውበት መነሻ፣ የተፈጥሮ ፈገግታ ጎልቶ የሚታይበት ወር በመሆኑ የኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች መነሻ መሆን ችሏል፡፡

በአጠቃላይ፣ ወርሃ ጥቅምት ተፈጥሮ እያሸበረቀች የምትፈካበት ወቅት ብቻ ሳይሆን፣ የከያኒያን የፈጠራ ስሜት የሚነቃቃበትና የሰው ልጅ የስሜት ህዋሳት በውበት የሚታደሱበት ወር ነው። ከኒል ያንግ እሸትንና ጨረቃን ካዋሃደው ዜማ እስከ ቫን ሞሪሰን “የጥቅምት መዝሙር”፣ ከነዋይ ደበበ “የጥቅምት አበባ” ህያው ውበት እስከ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ስዕላዊ የቃላት ድርሰት ድረስ ወርሃ ጥቅምት ዘመን ተሻጋሪ ለሆኑ የጥበብ ሥራዎች የሰው መንፈስ ማደሻ ምንጭ ሆኖ ዘልቋል። በመሆኑም ጥቅምት ከተፈጥሮ ወቅቶች አንዱ ብቻ ሳይሆን፤ ውበትን፣ ተስፋን፣ ፍቅርንና ትዝታን የመሸመኛ፣ የኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ስራዎች ማዕከል ለመሆን በቅቷል፡፡

የግዥ መለያ ቁጥር 001/19
ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ስር የሚገኘው የደጃ/ዘርዓይ ደረስ የመ/ደ/ ት/ቤት እና ጎላ ብርሃን አፀደ ህፃናት ት/ቤት በግልጽ ጨረታ ግዥዎችን መፈጸም ይፈልጋል፡፡

1.	የደንብ ልብሶች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	4000
2.	አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	4000
3.	አላቂ የህክምና ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	1000
4.	አላቂ የት/ት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	2000
5.	የፅዳት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	4000
6.	ልዩ ልዩ መሳሪያዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	4000
7.	ፕላንትና ማሽነሪ እና መሳሪያ ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	2000
8.	ለህንፃ፣ ማሽነሪ እና መሳሪያ ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	2000
9.	ፕላንትና ማሽነሪ እና መሳሪያ መግዣ የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	2000
10.	ህንፃ፣ ቁሳቁስና ተገጣጣሚ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	4000
11.	ልዩ ልዩ ክፍያዎች የጨረታ ማስከበሪያ በብር መጠን	1000

የተለያዩ ዕቃዎችን በግልፅ ጨረታ ላይ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ በዚህ ዘርፍ የተሰማራቹ ድርጅቶች በጨረታው እንድትሳተፉ እየጋበዝን፡፡

ለጨረታው የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው፣ የዘመኑን ግብር የከፈለ፣ የዕቃ አቅራቢዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያለው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
2. ተጫራቾች በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመስ ብር 400 (አራት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከት/ቤቱ ፋይናንስ የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኢንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት በት/ቤቱ ፋይናንስ ክፍል ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን በ10፡00 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ 10፡30 ሰዓት በት/ቤቱ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ናሙና (sample) ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ናሙናው ላይ ምንም ዓይነት የአድራሻ መግለጫ እንዳይደረግበት፡፡
7. ተጨራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ጥቅል ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
10. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡- ከተክለ ኃይማኖት አደባባይ ወደ ቴዎድሮስ አደባባይ ወደሚወስደው መንገድ ደቀ ማሐሪ ሆቴል ፊት ለፊት ስልክ ቁጥር 0111118126/ 0118 62 56 07

የደጃ/ዘርዓይ ድረስ አንደኛና መካከለኛ እና የጎላ ብርሃን ቅ/አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

እነ ኤልያስ ታደሰ ወያ (6 ሰዎች) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060706108 ሴሪ ቁጥር- C 01330519 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ7/15/8/12934/00 ሴሪ ቁጥር 002096 የተሰጠበት ቀን 23/09/2004 ዓ.ም በአቶ ንጉስ ስሜ ደሜ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

አመልካች ወ/ሮ ሰናይት ዮሃንስ ላንጋኖ በህጋዊ ወኪል በቀን 25/01/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር 10-1/92/12/6/27870/213343/01 የሴሪ ቁጥር 0161077 ወረዳ 10 የቦታው ስፋት 150 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፈቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ካርታው የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 በካርታ ቁጥር 016402 በሴሪ ቁጥር 001439 በአቶ ሰለሞን አድማሱ ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት ኦርጂናል ካርታ ኮፒ የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አመልካች ጊፍት ሪል እስቴት በቀን 29/01/19 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር የካርታ ቁጥር የካ/15512/13 የሴሪ ቁጥር 0134888 የቤቱ ስፋት 217.2 ሜ.ካ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለአዲስ ሚዲያ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል።

በመሆኑም ካርታው የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ ይሆናል።

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

አመልካች ሒዋን ፋንታሁን እና ቃሲም ቃድሮ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 በቀድሞ ካርታ ቁጥር 39963/A/46 በሴሪ ቁጥር 004350 በሒዋን ፋንታሁን እና ቃሲም ቃድሮ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/76/14-716/ሊ/ዕ/2467/01 ሴሪ ቁጥር 8082 በአቶ ቴዎድሮስ ሐጎስ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

የጥሪ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ ሠራተኞች ኃ/የተ/መሰረታዊ ሸማች ኀብረት ሥራ ማህበር መስከረም 10 ቀን 2019 ዓ.ም ኀብረት ሥራ ማህበሩ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ያስተላለፈ በመሆኑ ከመዝገብ ከመሰረዙ በፊት በኀብረት ሥራ አደረጃጀት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በኀብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ገንዘብ አለን የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ኀብረት ሥራ ማኅበሩ ጽ/ቤት በመገኘት ገንዘባችሁን ጠይቃችሁ መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እና በተባለው ጊዜ ውስጥ የማትወስዱ ከሆነ ኀብረት ሥራ ማህበሩ ተጠያቂ የማይሆን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ጽ/ቤት

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 468 የይዞታ ካርታ ቁጥር ወ12/12-95-569-9412/00 ሴሪ ቁጥር 0683985 በሀይሉ ካሳዬ ተመስገን እና አይናለም ካሳዬ ተመስገን ስም የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 25/01/2019 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይገፍዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ................................ ቀበሌ .... በአዲሱ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር .... በካርታ ቁጥር 16/73/6080/21679/0015133/02 በአቶ/ወ/ሮ /እነ በስራ ኮንስትራክሽን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገፍዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገፍዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በቤት ቁጥር 158 በካርታ ቁጥር 18/84/25037/00 በአቶ ጎሽሜ በላቸው እና በተጋሪ ወ/ሮ ዘውድነሽ አይተንፍሱ ስም በእጃቸው ላይ መገኘት የነበረበት ኦርጅናል ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አመልካች ሰንሻይን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን ረቡዕ ታህሳስ 5/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር ቦሌ8/94/5/2/48865/00 በሴሪ ቁጥር 122684 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ማህደር የተገኘ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይጻፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን።

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ ሳባ ማሞ አድማሱ ስም የተመዘገበ ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA000050906241 ሴሪ ቁጥር L 0168851 የሆነና የተሰጠበት ቀን 08/11/2016 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የጠፋባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ በቁጥር የካፖ//ለ/አ/ፖለ1428 በ 02/02/2019 ዓ/ም የተጻፈ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ ገነት አሰፋ በለጠ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር 01/66/8945/80367/01 ቁጥር ይዞታ የሴሪ ቁጥር 037654 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፍዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ወንድርላንድ ሪልእስቴት አክሲዮን ማህበር ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080105950010301 ሴሪ ቁጥር 0222388 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማንናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፍዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በአበሼ ረፊሳ ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የካርታ ቁጥር ወ2/ውዝ01/368/10317/00 ሴሪ ቁጥር 001247 የሆነ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ29/01/2019 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገፍዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አመልካች ወ/ሮ ፋኢዛ አሊ የወ/ሮ እሌኒ ስዩም ህጋዊ ወኪል በቀን 02/03/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር ቦሌ8/103/8/3/242000/00 ሴሪ ቁጥር 1532052 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፍዋለሁ አስይገፍዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን።

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 11 ሞሼ ተዘራ ባህታ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000051100657 የተሰጠበት ቀን 07/01/2009 ዓ.ም የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካ/ፖ/ለ/አ/ቀ3662/19 በቀን 22/01/2019 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡

ይህን በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አመልካች ጊፍት ሪል እስቴት በቀን 29/01/19 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የካርታ ቁጥር የካ/15449/13 ሴሪ 0134808 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፍዋለሁ አስይገፍዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን።

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

አመልካች ወ/ሮ ዋጋዬ ደቻሳ የመናብርት ሪልስቴት ህጋዊ ገዥ በቀን 02/02/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር የካ/219078/11 ሴሪ ቁጥር 1469074 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገፍዋለሁ አስይገፍዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን።

በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት

ወ/ሮ/ት ፀሀይ ቢተው ገድሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080800329020432 በሴሪ ቁጥሩ C 074876 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይገፍዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 09 ወ/ሮ/ወ/ሪት/አቶ/እነ/ ብዙአየሁ አደም መሀመድ በይዞታ መለያ ቁጥር AA0000709002152460002 በሴሪ ቁጥር 150870 የተመዘገበ ቤት- የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት

አፍሪካ በአዳዲስ የስፖርት ምዕራፎች

በሳህሉ ብርሃኑ

ዛሬ ላይ ስፖርት ከመዝናኛነትና ሜዳ ላይ ከሚደረግ ፉክክር ባለፈ አገራትን በዓለም ላይ በጥሩ ገጽታ የሚያስተዋውቅ፣ የምስል ግንባታን (Branding) የሚያጠናክር እና የታላቅ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ መገለጫ ሆኗል። በተለይም ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነቶችን ለሚያስተናግዱ አገራት ከውድድሮቹ ድምቀት በላይ የኢኮኖሚ፣ የመሠረተ-ልማት እና የቱሪዝም ልማት በሮችን የሚከፍት ትልቅ ዕድል ነው።

“The Economic Effects of a Marathon as a Sport Tourism Event” ጥናታዊ ጽሑፍ ፀሐፊው ግሪጎሪ ፓፓኒኮስ በተለይም ባለፉት አስርት ዓመታት እንደ ማራቶን ያሉ ስፖርታዊ ፌስቲቫሎች ብዙ ጎብኚዎችን ከመሳባቸው በተጨማሪ ሀገርን ማስተዋወቂያ መሳሪያ በመሆን ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው ይላሉ፡፡

አንድ ከተማ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ሁነቶችን ማስተናገድ መቻሏ ከስፖርታዊ ድምቀት ባለፈ ብዙ ፋይዳ አለው። እንዲህ ያሉ መድረኮች የአንድን ከተማ የመሠረተ-ልማት ግንባታ የሚያፋጥኑ፣ የቱሪስት ፍሰትን የሚጨምሩና የንግድ እንቅስቃሴን የሚያነቃቁ ሲሆኑ፣ ከተማዋን በዓለም መድረክ ተመራጭ መዳረሻ በማድረግ ረገድም ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

በተለይም ለዓመታት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ በተሳትፎ ብቻ የቆየችው አህገረ አፍሪካ አሁን ላይ ውድድሮች ወደማስተናገዱ መጥታለች፡፡ በአፍሪካ ምድር ሲካሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነው የሴኔጋል ዳካር 2026 የወጣቶች ኦሎምፒክ ጨዋታዎች፣ በአፍሪካ ምድር ሲካሄድ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሆነው የኬንያ ናይሮቢ 2029 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና እና አሁን ደግሞ የፎርሙላ 1 ግራንድ ፕሪን ሩዋንዳ እንድታዘጋጅ ተወስኗል፡፡

የዓለም አትሌቲክስ በሃንጋሪ ቡዳፔስት ባካሄደው 242ኛው የካውንስል ስብሰባ፣ የኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ የ2029ኙን የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በአፍሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ እንድታዘጋጅ መወሰኑ የሚታወስ ነው፡፡ ናይሮቢ ይህን ታላቅ ድግስ የማዘጋጀት ዕድል ያገኘችው ቀደም ሲል ከ18 ዓመት በታች የዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና እና የኪፕ ኬይኖ ክላሲክ ውድድሮችን በብቃት በማዘጋጀቷ እንዲሁም ከታንዛኒያ እና ዑጋንዳ ጋር በጣምራ የ2027ቱን የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት በመመረጧ እንደሆነ ተገልጿል።

ኬንያ የ2029ኙን የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና እንድታሰናዳ መመረጧን ተከትሎ ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ባስተላለፈው መልዕክት፣ በዓለም ትልቁ የአትሌቲክስ ውድድር መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ምድር መሰናዳቱ አስደናቂ ዜና መሆኑን ተናግሯል፡፡ በዚህም ኩራት እንደተሰማው ገልፆ፣ ናይሮቢ ውድድሩን የማሰናዳት ዕድል እንድታገኝ ድምፃቸውን ለሰጡም ምስጋናውን አቅርቧል። “የመረጣችሁት ኬንያን ብቻ ሳይሆን ድፍን አፍሪካን ነው” ብሏል።

ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

በሌላው ዓለም በስፋት ይካሄዱ የነበሩ የስፖርት ውድድሮች ወደ አፍሪካ መምጣት ጀምረዋል

በሩዋንዳ በተካሄደው የዓለም አቀፉ የአውቶሞቢል ፌዴሬሽን (ኤፍአይኤ) ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ይፋ እንደተደረገው የፎርሙላ ዋን ግራንድ ፕሪክስ ውድድር በሩዋንዳ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ በኪጋሊ እየተደረገው ያለው የኤፍዋን ጉባኤ በአፍሪካ ሲካሄድ የመጀመሪያው ነው ያሉት የኤፍአይኤ ፕሬዝዳንት ሞሐመድ ቤን ሱላይም የሩዋንዳን በሞተር ስፖርት ላይ እያደገ ያለውን ተፅዕኖ አሞካሽተው የአህጉሪቷን ወደፊት በሞተር ስፖርት ላይ ያላትን መልካም ተስፋ ተናግረዋል። ደቡብ አፍሪካ ካዘጋጀችው የጎርጎሮሳዊያኑ 1993 ውድድር በኋላ በአፍሪካ የሚደረግ ውድድር ይሆናል።

በዓለም አቀፉ የመኪና ፌዴሬሽን (FIA) የሚመራውና የከፍተኛ ፍጥነት የመኪና ውድድሮች ጥግ የሆነው ፎርሙላ 1 (Formula 1)፣ ከሶስት አስርት ዓመታት ጥበቃ በኋላ ወደ አፍሪካ ምድር መመለሱ ለአህጉሪቱ ታሪካዊ ሁነት ነው። በሩዋንዳ ቡጌሴራ በሚገነባ ዘመናዊ የውድድር ማዕከል በ2030ዎቹ መጀመሪያ ላይ እንዲካሄድ የተወሰነው ታላቅ አህጉራዊ ዝግጅት፣ ከስፖርታዊ ድምቀቱ ባለፈ የአፍሪካን ዓለም አቀፍ ገጽታ የሚያድስ እንደሚሆን ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ የቱሪስት ፍሰትንና የውጭ ኢንቨስትመንትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያነቃቃ እንዲሁም አዳዲስ የስራ ዕድሎችንና የክህሎት ልማትን የሚያስገኝ ታላቅ የዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ መጫወቻ ካርድ ነው።

የስፖርቱ ዓለም ዓይን ያረፈባት አዲስ አበባም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የዓለም አቀፍ ውድድሮች መድረክ እየሆነች መጥታለች፡፡ የግራንድ ፕሪ የጎዳና ላይ ሩጫ፣ የሼክ ዛይድ የበጎ አድራጎት ሩጫ፣ በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የሲቲ ማውንቴን ባይክ (ተራራ ብስክሌት) ውድድር እና የምስራቅ አፍሪካ የእጅ ኳስ ውድድር በስኬት ማስተናገዷ ለዚህ ምስክር ናቸው።

በተለይም በከተማ ኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች አማካኝነት መንገዶች ለሰውና ለተሽከርካሪ ምቹ እንዲሆኑ እየተደረገ ሲሆን፣ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ዙሪያ ያሉ ዘመናዊና ሰፋፊ አደባባዮች መገንባታቸው ከተማዋ ለትልልቅ ህዝባዊና ስፖርታዊ ሁነቶች ያላትን ዝግጁነት ከፍ አድርጎታል።

ከዚህም በተጨማሪ የወንዞች ዳርቻ ልማትና የመናፈሻዎች መስፋፋት ከተማዋን ለዓለም አቀፍ ስፖርተኞችና ጎብኚዎች ሳቢ ከማድረጋቸውም በላይ፣ አዲስ አበባን በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ እየተከናወነ ያለውን ጥረት ያሳያሉ።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅርቡ ያስተናገደችው የነሃስ ደረጃ ያለው የአንድ ቀን የግራንድ ፕሪ ውድድር በዓለም አትሌቲክስ ከፍተኛ አድናቆት እንዳስገኘላት የሚታወስ ነው። በዚህም ስኬት መነሻነት ውድድሩ በቀጣይ ዓመት በወርቅ ደረጃ እንዲካሄድ ተወስኗል። ይህም አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ውድድሮችን የማስተናገድ ብቃቷን በተግባር ያረጋገጠችበት አጋጣሚ ሆኗል።

ከተማዋ በውበት፣ በንጽህና እና በዘመናዊ መሰረተ ልማቶች እያገኘችው ያለው ዓለም አቀፍ እውቅና፣ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮችን የማስተናገድ አቅሟን በከፍተኛ ደረጃ አሳድጎታል። በርካታ ዓለም አቀፍ የስፖርት ጋዜጠኞች አዲስ አበባን ለየት የሚያደርጋት ቀዳሚው ምክንያት በከፍታ ቦታ ላይ የመገኘቷ ተፈጥሯዊ ጸጋ ከዘመናዊ የከተማ ውበት ጋር መጣመሩ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2028 የሚካሄደውን የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት በይፋ ጥያቄ ያቀረበች ሲሆን፣ ይህም አህጉሪቱ በጉጉት የምትጠብቀውን ትልቁን የእግር ኳስ ውድድር ከ50 ዓመታት በላይ በኋላ ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ እየተደረገ ያለ ጥረት ጭምር ነው።